# የጳውሎስ
# የእስር ቤት ደብዳቤዎች

## ትምህርት ሁለት
## ጳውሎስ እና የቆላስይስ ሰዎች

## Paul's Prison Epistles
## Lesson Two
## Paul and the colossians

ተርጓሚ፡ እሸቴ በለጠ
Translator: Eshete Belete

THIRD MILLENNIUM MINISTRIES
Biblical Education. For the World. For Free.

© 2010 by Third Millennium Ministries
www.thirdmill.org

# እናስተዋውቅዎ

የሰርድ ሚሊኒየም ሚኒስትሪ እንደ አውሮፓውያኑ አቆጣጠር በ1997 ዓ.ም. ተመሠረተ፡፡ ይህ አገልግሎት አትራፊ ያልሆነ ድርጅት ሲሆን፣ መጽሐፍ ቅዱሳዊ አስተምህሮዎችን ለመላው ዓለም በነጻ ለማዳረስ የተቋቋመ ነው፡፡ በዓለም አቀፍ ደረጃ ያለውን ጤናማ፣ መጽሐፍ ቅዱሳዊ - መሠረት ያለው ክርስቲያናዊ የአመራር ስልጠና ፍላጎት ምላሽ ለመስጠት፣ ምንም ዓይነት የስልጠና ግብዓቶች የማግኘት እድል ለሌላቸው ክርስቲያን መሪዎች የሴሚነሪ ሥርዓተ-ትምህርቶችን በማዘጋጀት እናሰራጫለን፡፡ ሰርድ ሚሊኒየም ሚኒስትሪ በመላውም ዓለም ለሚገኙ ክርስቲያን መሪዎችና ፓስተሮች የተመጣጠነ ዋጋ ያለው፣ በደጋፊዎች የሚታገዝ፣ ለተጠቃሚው ምቹ፣ በልዩ ልዩ የመገናኛ ብዙሃን ዘዴዎች የታገዘ ሥርዓተ-ትምህርት በአምስት ቋንቋዎች (በእንግሊዝኛ፣ በስፓኝ፣ በራሺያኛ፣ በማንዳሪን ቻይንኛ እና በአረብኛ) አስተርጎሞ አሰራጭቷል፡፡ ሁሉም ትምህርቶች የተጻፉት፣ የተዘጋጁት እና የታተሙት በአገልግሎቱ ውስጥ ሲሆን በ The History Channel©. In 2009 ካሉት ጋር በቅርፅና በጥራት ተመሳሳይነት አላቸው፡፡ የሰርድ ሚሊኒየም ሥራ ማለትም ጥራት ላለው የማስተማሪያና የአኒሜሽን የቪዲዮ ፕሮዳክሽን ሥራዎቹ ሁለት የቴሊ አዋርድ ሽልማቶችን ተቀብሏል፡፡ የማስተማሪያ ግብዓቶቻችን በዲቪዲ፣ በህትመት፣ በኢንተርኔት ማስተላለፊያ ዘዴዎች፣ በሳተላይት የቴሌቪዥን ስርጭት፣ በራዲዮና በቴሌቪዥን ስርጭቶች ለማቅረብ በሚያስችል መልክ የተቀረፁ ናቸው፡፡

ስለ አገልግሎታችን የበለጠ መረጃ ለማግኘትና እንዴት የአገልግሎቱ ተጠቃሚ መሆን እንደምትችሉ ማወቅ ከፈለጋችሁ፣ www.thirdmill.org የተሰኘውን ድረ-ገጽ ይጎብኙ፡፡

© 2010 by Third Millennium Ministries
www.thirdmill.org

# ማውጫ

1. **መግቢያ**
2. **ዳራ**
    - ግንኙነቶች
        - ቤተክርስቲያን
        - ግለሰቦች
    - በቆላስይስ የነበሩ ችግሮች
    - የግሪክ ፍልስፍና
    - የአይሁድ ህግ
    - መንፈሳዊ ኃይላት

3. **አወቃቀርና ይዘት**
    - ሰላምታ
    - ማበረታቻዎች
    - የመደምደሚያ ሰላምታ
    - የክርስትና ገናንነት
        - የክርስቶስ ገናንነት
        - የክርስቶስ አገልጋዮች ገናንነት
        - በክርስቶስ የመዳን ገናንነት
        - የክርስቲያናዊ አኗኗር ገናንነት

4. **ዘመነኛው ተዛምዶ**
    - ለክርስቶስ ታማኝ መሆን
    - መንፈሳዊ ዒላማ/ትኩረት

5. **ማጠቃለያ**

© 2010 by Third Millennium Ministries
www.thirdmill.org

# 1. መግቢያ

ማርክ ትዌይን በተሰኘው አሜሪካዊ ጸሐፊ የተጻፈ "ልዑሉና የኔቢጤው ድሃ" የተሰኘ ዕውቅ ታሪክ አለ፡፡ በታሪኩ ውስጥ፣ ልዑሉ ደሃውን ለማኝ ወደ ቤተመንግሥቱ ይጋብዘዋል፣ ለጨዋታም ያህል ሁለቱ ልብሳቸውን ይለዋወጣሉ፡፡ እንደ አለመታደል ሆኖ ልዑሉ፣ በስህተት እንደ ለማኝ ይቆጠርና ከቤተመንግሥት ይባረራል፡፡ ለማኙ ደግሞ በሌላው ጎን፣ በስህተት እንደ ልዑል ይቆጠርና በቤተመንግሥት ውስጥ እንደ ልዑል መኖር ይጀምራል፡፡

እንግዲህ፣ በዚህ ታሪክ ውስጥ፣ ልዑሉም ሆነ የኔ ቢጤውም ደሃ ሰዎች ማንነታቸውን በማምታታቸው ይገረማሉ፡፡ ልዑሉ ከቤተመንግሥት እንደሚባረር ቢያውቅ ኖሮ፣ ከለማኙ ጋር ልብሱን የመቀያየር ጨዋታ ለመጫወት ፈቃደኛ ባልሆነም ነበር፡፡ ይህንን የመሰለ ልብስን የመለዋወጥ ቀላል ጨዋታ፣ ያንን ሁሉ ትልቅ ኃይልና ጥቅም ለማሳጣት ብቃት ሊኖረው ከቶውኑ አይችልም፡፡ በአንዳንድ መንገዶች፣ በመጀመሪያው ክፍለ ዘመን በነበረችው የቆላስይስ ቤተክርስቲያን ውስጥ የነበሩት ሁኔታዎች "ልዑሉና የኔቢጤው ድሃ" ከተሰኘው ታሪክ ጋር የሚመሳሰልበት ሁኔታ አለ፡፡ በቆላስይስ ይኖሩ የነበሩ ክርስቲያኖች በአህዛብ የአምልኮ ወግ ውስጥ እንዲሳተፉ ይበረታቱ ነበር፡፡ ስለዚህ፣ ጳውሎስ እነርሱ በክርስቶስ ስለተቀበሉት እጅግ አስደናቂ ብልጥግናና ንግሥና ሊያሳስባቸው እና ጣዖታት ይሰጧችኋል ተብሎ ለሚነገራቸው ከንቱ ማታለያ ልባቸውን እንዳይሰጡ ሊያስጠነቅቃቸው ይጽፍላቸዋል፡፡

ይህ አሁን የምንከታተለው "የጳውሎስ የእስር ቤት ደብዳቤዎች" ተብሎ ከሚጠራው ተከታታይ ትምህርታችን ሁለተኛው ትምህርት ሲሆን፣ "ጳውሎስና የቆላስይስ ሰዎች" የሚል ርዕስ ሰጥተነዋል፡፡ በዚህ ትምህርት ጳውሎስ ለቆላስይስ ሰዎች የጻፈውንና የቃለ እግዚአብሔርነት ሥልጣን የተሰጠውን ደብዳቤ እናጠናለን፡፡ በዚህ ደብዳቤ ውስጥ፣ እንደምንመለከተው፣ በክርስቲያናዊ አምልኮ ውስጥ ሰርጎ ለገባውና ለትናንሽ መንፈሳውያን ኃይላት ክብር እንዲሰጥ ለሚጋብዘው የሐሰት አስተምህሮ ጳውሎስ ጠንካራ ምላሽ ይሰጣል፡፡

ጳውሎስና የቆላስይስ ሰዎች የተሰኘው ትምህርታችን በሦስት ክፍሎች ይከፈላል፡፡ አንደኛ፣ ጳውሎስ ለቆላስይስ ሰዎች የጻፈውን መልእክት ዳራ እንመረምራለን፡፡ ሁለተኛ፣ ለቆላስይስ የጻፈውን መልእክት አወቃቀርና ይዘት እንቃኛለን፡፡ ሦስተኛ ደግሞ፣ በደብዳቤው ዘመነኛ ተዛምዶ ላይ እናተኩራለን፡፡ አስቀድመን ጳውሎ ለቆላስይስ ሰዎች የጻፈውን መልእክት ዳራ እንመልከት፡፡

# 2. ዳራ

ጳውሎስ የኢየሱስ ክርስቶስ ሐዋርያ ሲሆን፣ መልእክቶችን መጻፍ እንደ ክርስቶስ አምባሳደር የአገልግሎት ሥልጣኑ አካል ነው፡፡ የሐዋርያነቱ አንዱ ክፍል የአብያተክርስቲያናትና የግለሰቦች እረኛ መሆን ነው፡፡ እናም ስለዚህ የጳውሎስ ደብዳቤዎች የሥልጣናዊ አስተምህሮዎች ስብስቦች ብቻ አይደሉም፡፡ ይልቁኑም፣ ለሚጽፍላቸው አብያተክርስቲያናትና ግለሰቦች ካለው ፍቅር እና ግድ መሰኘት የመነጨ የግል ወዳጅነትና የእረኝነት ደብዳቤዎች ናቸው፡፡ በተጨማሪም የጳውሎስ መልእክቶች "ወቅታዊ" ናቸው፡፡ ያም ማለት፣ በአንድ ውሱን ዘመን እና ስፍራ ለተነሱ ጉዳዮች ምላሽ ለመስጠት የተፃፉ ናቸው ማለት ነው፡፡

ስለዚህ፣ ጳውሎስ ለቆላስይስ ሰዎች የጻፈውን ደብዳቤ በምናነብበት ወቅት፣ ጳውሎስ ደብዳቤውን እንዲጽፍ ስላነሳሳው ሁኔታ አንድ ነገር ማወቃችን ጠቃሚ ነው፡፡ ይህንንም ለመረዳት፡ የቆላስይስ ሰዎች ምን ዓይነት ችግሮች ነበሩባቸው? ጳውሎስ ለእነርሱ እንዲጽፍ ያነሳሳው ምንድን ነው? የሚሉ ጥያቄዎችን መጠየቅ

© 2010 by Third Millennium Ministries
www.thirdmill.org

ይገባናል፡፡ ጳውሎስ ለቆላስይስ ሰዎች የጻፈውን ደብዳቤ ዳራ በሁለት አቅጣጫዎች እንመለከተዋለን፡ አንደኛ፣ ጠቅለል ባለ መንገድ ከቆላስይስ ቤተክርስቲያን ጋር ደግሞም በቤተክርስቲያኒቱ ውስጥ ከነበሩ ግለሰቦች ጋር የነበረውን ግንኙነት የሚያሳዩ ጥቂት ዝርዝር ጉዳዮችን እንጠቃቅሳለን፡፡ ሁለተኛ ደግሞ፣ ጳውሎስን ያሳሰቡትን ጥቂት ችግሮች እንመረምራለን፡፡ እስኪ ጳውሎስ ከቆላስይስ ሰዎች ጋር የነበረውን ግንኙነት በመመልከት እንጀምር፡፡

# ግንኙነቶች

ጳውሎስ በቆላስይስ ከሚገኙ ክርስቲያኖች ከሁሉም ጋር እኩል የሆነ ግንኙነት አልነበረውም፣ ስለዚህ አስቀድመን በጠቅላላው ከቤተክርስቲያኒቱ ጋር በነበረው ግንኙነት ላይ፣ ከዚያም ከአንዳንድ ግለሰቦች ጋር በነበረው ግንኙነት ላይ እናተኩራለን፡፡ አስቀድመን ከቆላስይስ ቤተክርስቲያን ጋር የነበረውን ግንኙነት በመመልከት እንጀምር፡፡

## ቤተክርስቲያን

የቆላስይስ ከተማ የሮማ ግዛት በሆነችው በእስያ ጠቅላይ ግዛት ፊርጊያ ተብሎ በሚጠራው አካባቢ የምትገኝ ከተማ ናት፡፡ ከተማይቱ የተመሰረተችው በሊከስ ሸለቆ ሲሆን፣ ትልቅና ይበልጥ ታዋቂ ከሆነችው የሎዶቅያ ከተማ በስተምሥራቅ ወገን ትገኛለች፡፡ ቆላስይስ በንጽጽር አነስ የምትል ከተማ ነች፡፡ በዘመኑ በነበረው ፖለቲካዊና ኤኮኖሚያዊ መመዘኛ፣ የጳውሎስን እስትንፋሰ መለኮታዊ እውቅና ያገኘ ደብዳቤ ሊጻፍላት የሚያስችል ግዝፈት አልነበራትም ወሳኝነቷም እምብዛም ነበር፡፡ ጳውሎስ የቆላስይስን ቤተክርስቲያን አልጎበኘም፣ የሆነ ሆኖ ግን ስለ እነርሱ በጣም ግድ ይለው ነበር፡፡ በቆላስይስ ምዕራፍ 2 ቁጥር 1 የተናገራቸውን ቃላት አድምጡ፡

> ***ስለ እናንተና በሎዶቅያ ስላሉት ፊቴንም በሥጋ ስላላዩት ሁሉ እንዴት ያለ ትልቅ መጋደል እንዳለኝ ልታውቁ እወዳለሁና፤ (ቆላስይስ 2፡1)***

ጳውሎስ በሁለተኛው ሚሲዮናዊ ጉዞው ወቅት በፊርግያ በኩል አልፏል፣ በሆነ ምክንያት ግን የቆላስይስን ቤተክርስቲያን አልጎበኘም፡፡ ቤተክርስቲያኒቱ በዚያ ስፍራ ከመመሥረቷ አስቀድሞ ወደ ቆላስይስ ሄዶ እንደነበር ይገመታል፡፡ ወይም ከተማይቱን የመጎብኘት እድል ቢያገኝም ምናልባት ቤተክርስቲያኒቱን የማግኘት ዕድል ሳያገኝ ቀርቶም ይሆናል፡፡ አለበለዚያ ደግሞ የቆላስይስን ከተማ ጨርሶውኑ አልረገጠም ይሆናል፡፡ ምንም ይሁን ምን፣ ጳውሎስ ከአማኞቹ አብዛኞቹን ሰዎች በግል አያውቃቸውም ነበር፡፡

ሆኖም፣ ጳውሎስ ለቆላስይስ ሰዎች ከጻፈው ዝርዝር ደብዳቤ፣ በቆላስይስ ይኖር ለነበረው ለፊልሞና ከጻፈው ደብዳቤ ከእነርሱ ጋር ስለነበረው ግንኙነት ጥቂት ነገሮችን መረዳት እንችላለን፡፡ አንዱ ነገር፣ ጳውሎስ ከቆላስይስ ሰዎች ጋር ይገናኝ የነበረው የቆላስይስ ሰዎች በነበሩት ኤጳፍራ፣ ፊልሞና እና አናሲሞስ እና ቲኪቆስ በሚባለው መልእክተኛው አማካይነት በተዘዋዋሪ ነበር፡፡

ሁለተኛ፣ ምንም እንኳን ፊት ለፊት ባይተያዩም፣ የቆላስይስ ሰዎችና ጳውሎስ መልእክት ይለዋወጡ ነበር፡፡ ለአብነት ያህል፣ ኤጳፍራ ስለ ቆላስይስ ሰዎች ለጳውሎስ መረጃ ይሰጠው ነበር፡፡ ደግሞም ጳውሎስ ቢያንስ የጳውሎስ መልእክት ወደ ቆላስይስ ሰዎች የተሰኘ አንድ የአዲስ ኪዳን መልእክት ጽፎላቸዋል፡፡

© 2010 by Third Millennium Ministries
www.thirdmill.org

ሦስተኛ፣ ጳውሎስና የቆላስይስ ሰዎች አንዳቸው ሌላቸውን አገልግለዋል፡፡ ለምሳሌ፣ ጳውሎስ ስለ እነርሱ በእስር ቤት ከመጋደሉ ባሻገር፣ ለቆላስይስ ሰዎች በተለይ ይጸልይላቸው ነበር፡፡ በቆላስይስ ምዕራፍ 1 ቁጥር 9 እንዲህ ተጽፏል፡

> *ስለዚሁ እኛ ደግሞ ይህን ከሰማንበት ቀን ጀምረን የፈቃዱ እውቀት መንፈሳዊ ጥበብንና አእምሮን ሁሉ እንዲሞላባችሁ እየለመንን፥ ስለ እናንተ ጸሎትን አልተውንም፤ (ቆላስይስ 1፡9)*

ጳውሎስ ለእነርሱ እጅግ የሚጠቅማቸውን በረከት እንዲያገኙ፣ በተለየ መንገድ አዘውትሮ ስለ እነርሱ ይጸልይላቸው ነበር፡፡

አራተኛ፣ የቆላስይስ ሰዎችም ጳውሎስን አገልግለውታል፡፡ ጳውሎስ ለቆላስይስ ሰዎችና ለፊሊሞና ከጻፋቸው ደብዳቤዎቹ እንደምንረዳው፣ ኤጳፍራና አናሲሞስ የተሰኙ የቆላስይስ ሰዎች እስር ቤት ሄደው ጳውሎስን ጎብኝተውታል፡፡ እናም የቆላስይስ ሰዎች መልእክተኞችን ወደ ጳውሎስ እስከላኩ ድረስ፣ ለእርሱ እንደሚጸልዩለት መገመት ምክንያታዊ ነው፡፡

በአጭሩ፣ ምንም እንኳን ጳውሎስ ከቆላስይስ አማኞች አብዛኞቹን ፊት ለፊት ባያገኛቸውም፣ አንዳቸው ለሌላቸው ግድ የሚሰኙ ሲሆን፣ ግንኙነታቸውንም እውነተኛና ቁም ነገር አዘል የሚያደርገው አንድ የጋራ ጉዳይ ነበራቸው፡፡

ጳውሎስ ከቆላስይስ ቤተክርስቲያን ጋር የነበረውን ግንኙነት ባህርይ ከተመለከትን፣ ከእርሱ ጋር ትውውቅ ከነበራቸውና በቆላስይስ ቤተክርስቲያን ይገኙ ከነበሩ አንዳንድ ግለሰቦች ጋር የነበረውን ግንኙነት ደግሞ እንመልከት፡፡

## ግለሰቦች

ጳውሎስ ከቆላስይስ የሆኑ በርካታ ወዳጆች ነበሩት፡፡ እነዚያም ሰዎች እንዲያው የሚተዋወቁ ብቻ ሳይሆኑ፣ የቅርብ ወዳጆቹ፣ አብዛኞቹ ደግሞ በወንጌል አገልግሎት ከጳውሎስ ጋር አብረው የተጋደሉ ናቸው፡፡ ከእነዚህም ወዳጆቹ ሦስቱ፣ ፊልሞና፣ አፍብያ፣ አክርጳ ናቸው፡፡ በፊልሞና ቁጥር 1 እና 2 በሰላምታው ውስጥ ጳውሎስ ያሰፈረውን አድምጡ፡

> *የክርስቶስ ኢየሱስ እስር ጳውሎስ ወንድሙም ጢሞቴዎስ፥ ለተወደደውና አብሮን ለሚሠራ ለፊልሞና፥*
> *ለእኅታችንም ለአፍብያ፥ ከእኛም ጋር አብሮ ወታደር ለሆነ ለአርክጳ፥ በቤትህም ላለች ቤተ ክርስቲያን፤ (ፊልሞና 1-2)*

ቢያንስ፣ ፊልሞና የጳውሎስ የቅርብ ወዳጅ ነበር፡፡ ደግሞም ጳውሎስ አፍብያን በስም ሲጠቅስ እርሷን የሚያወቃት ይመስላል፡፡ በርካታ ምሁራን እንደሚያምኑት፣ ከፊልሞና ቤተሰብ አንዷ እንዲያውም ባለቤቱ ልትሆን ትችላለች፡፡ አክርጳ በቤተክርስቲያን ውስጥ ስፍራ ያለው ሰው ከሆነ፣ ጳውሎስ እርሱን መጥቀሱ ያለውን ከበሬታ ለማሳየት ይሆናል፡፡ ግን ከዚህ ይልቅ የሚቀርበው እርሱም የፊልሞና ቤተሰብ አባል ምናልባትም ልጁ ሊሆን ይችላል የሚለው ነው፡፡

© 2010 by Third Millennium Ministries
www.thirdmill.org

ከጳውሎስ የቆላስይስ ወዳጆች ሌላኛው አጳፍራ ነው፡፡ ጳውሎስ ኤጳፍራን የሚገልጠው አብሮኝ ሠራተኛ እና እሥረኛ በማለት ሲሆን፣ የክርስቶስ ታማኝ አገልጋይ በማለትም ኤጳፍራን ይጠቅሰዋል፡፡ ጳውሎስ መልእክቱን ለቆላስይስ ሰዎች በጻፈበት ወቅት ኤጳፍራ ከጳውሎስ ጋር በእስር ቤት ቆይቷል፡፡

የጳውሎስ ወዳጅ አናሲሞስም የቆላስይስ ሰው ነበር፡፡ ከጌታው ከፊልሞና ከኮበለለ በኋላ ጳውሎስን ፍለጋ የሄደ ባርያ ሲሆን፣ በመጨረሻም በእስር ቤት ውስጥ የጳውሎስ አገልጋይ ሆኖ ነበር፡፡

አብዛኞቹ የጳውሎስ ወዳጆች በአንድ መልኩ ከፊልሞና ጋር ትስስር ያላቸው ናቸው፡፡ ግንኙነታቸው ምንም መልክ ይኑረው ምንም፣ ጳውሎስ ከጠቅላላው ቤተክርስቲያን ጋር ከነበረው ግንኙነት ይልቅ ከእነዚህ ወዳጆቹ ጋር በግል የነበረው ግንኙነት የቅርብ ግንኙነት ነበር፡፡ ለቆላስይስ ሰዎች የጻፈው ደብዳቤ በግልፅ እንደሚያሳየን ግን፣ ከእነዚህ ወዳጆቹ ጋር ያለው ግንኙነት በቆላስይስ ለሚኖሩ አማኞችም በጠቅላላ ፍቅሩ እንዲጨምር አድርጎታል፡፡

እንግዲህ ጠቅለል አድርገን ስንናገር፣ ጳውሎስ ከቆላስይስ ቤተክርስቲያን ጋር የነበረው የግል ቅርርብ ልከኛ ነበር፡፡ ሆኖም ደግሞ ለበርካቶቹ የቤተክርስቲያኒቱ አባላት እጅግ ግድ ይሰኝ ነበር፡፡ ሐዋርያ በመሆኑ ብቻ ሳይሆን፣ ከወዳጆቹ ጋር ከነበረው ጥብቅ ወዳጅነት የተነሳ ለቤተክርስቲያኒቱ ጥልቅ ስሜት ነበረው፡፡

ጳውሎስ በጥቅሉ ከቆላስይስ ሰዎች ጋር እና በቆላስይስ ከሚገኙ ግለሰቦች ጋር ስለነበረው ግንኙነት ስንመለከት ቆይተናል፣ አሁን ደግሞ ጳውሎስን ያሳሰቡት የነበሩና በቆላስይስ የተከሰቱ ችግሮችን ለመመርመር እንዘጋጃለን፡፡ ምን ችግሮች ነበሩባቸው? ጳውሎስ ለእነርሱ እንዲጽፍ ምን አነሳሳው?

## በቆላስይስ የነበሩ ችግሮች

ጳውሎስ በእስር ላይ በነበረበት ወቅት፣ ኤጳፍራ የተሰኘና ነዋሪነቱ በቆላስይስ ከተማ የሆነ ሰው ጎብኝቶት ነበር፡፡ ኤጳፍራም የቆላስይስን ቤተክርስቲያንን ጨምሮ፣ በሊከስ ሸለቆ የሚገኙ አብያተክርስቲያናትን እየተፈታተናቸው ስላለው የሐሰት ትምህርት ለጳውሎስ ነገረው፡፡ ስለዚህም ቤተክርስቲያንን ከእነዚህ የሐሰት ትምህርቶች ለመከላከል፣ ጳውሎስ ለቆላስይስ ሰዎች ደብዳቤ ጻፈላቸው፡፡ ወደ ቆላስይስ ቤተክስቲያን ስለገባው የስህተት አስተምህሮ ዝርዝር ነገሮችን ባናውቅም፣ የጳውሎስ ደብዳቤ ግን ስለማንነታቸው በርካታ ነገሮችን አሳውቆናል፡፡

በመጀመሪያ፣ በቆላስይስ የነበረው የሐሰት ትምህርት የክርስትናን እምነት ከግሪክ ፍልስፍና ጋር የቀላቀለ ነበር፡፡ ሁለተኛ፣ በአይሁድ ህግ ላይ ያለመጠን የተደገፈ ነበር፡፡ ሦስተኛ ደግሞ፣ ክርስቲያኖች ሊያከብሯቸውና ሊለማመኗቸው የሚገቡ በርካታ አማልክት አሉ የሚል ነበር፡፡ ከግሪክ ፍልስፍና ጋር የሚዛመደውን የዚህን አስተምህሮ ገፅታ በመመልከት እንጀምር፡፡

### የግሪክ ፍልስፍና

በመጀመሪያው ክፍለ ዘመን በነበረው የሜድትራኒያን ዓለም ውስጥ፣ በሃይማታዊው አመለካከትና በመደበኛው አዕምሮአዊ እውቀት መካከል ግልፅ ያለ የመለያ መስመር አልነበረም፡፡ በውጤቱም፣ ፍልስፍና የሚለው ቃል በባእድ አምልኮ አራማጆች፣ በተለይም በሃይማኖታዊ ትውፊቶች ላይ በተመሠረቱት ዘንድ በስፋት አገልግሎት ላይ ይውል ነበር፡፡ በተደጋጋሚም እነዚህ ትወፊቶች፣ ለየት ያሉ ምሥጢራዊ ነገሮችንና መብቶችን፣ በተጨማሪም ድብቅ እውቀትንና ጥበብን ያካትቱ ነበር፡፡ የሚያሳዝነው ግን፣ እነዚህ የባዕድ አምልኮ

ፍልስፍናዎች በቆላስይስ ቤተክርስቲያንም ውስጥ ሰርገው የሚገቡበት ቀዳዳ ማግኘታቸው ነው፡፡ በቆላስይስ ምዕራፍ 2 ከቁጥር 1 እስከ 4 ጳውሎስ ስለዚህ ጉዳይ የነበረውን ስጋት እንመለከታለን፡

*ስለ እናንተና በሎዶቅያ ስላሉት ..... ሁሉ እንዴት ያለ ትልቅ መጋደል እንዳለኝ ልታውቁ እወዳለሁና፤*
*የእግዚአብሔርንም ምሥጢር እርሱንም ክርስቶስን እንዲያውቁ ኢጋደላለሁ፤*
*የተሰወረ የጥበብና የእውቀት መዝገብ ሁሉ በእርሱ ነውና።*
*ማንም በሚያባብል ቃል እንዳያስታችሁ ይህን እላለሁ። (ቆላስይስ 2፡1-4)*

በዚህ ስፍራ የምንመለከታቸው የጳውሎስ ቃሎች የቆላስይስ ሰዎች የግሪክ ፍልስፍናና ሃይማኖት ያከብሩት ለነበረው ለምሥጢር፣ ለጥበብና ለእውቀት ከፍ ያለ ስፍራ ይሰጡ እንደነበር ያመለክታሉ፡፡ ስለዚህም፣ በቆላስይስ የነበሩ የሐሰት መምህራን ለሚያቀርቡት መከራከሪያ ምላሽ ለመስጠት፣ እውነተኛው ምሥጢር፣ ጥበብና እውቀት የሚገኘው በክርስቶስ ብቻ እንጂ በአህዛብ ሃይማኖት እንዳልሆነ ጳውሎስ አጽንዖት ሰጥቶ ያሳስባል፡፡

ከዚም በቆላስይስ ምዕራፍ 2 ቁጥር 8 ውስጥ፣ ጳውሎስ ፍጹም እርግጠኝነት በሞላበት አገላለፅ በአህዛብ ፍልስፍና ላይ በማነጣጠር ይኮንነዋል፡፡

*እንደ ክርስቶስ ትምህርት ሳይሆን፥ እንደ ሰው ወግና እንደ ዓለማዊ እንደ መጀመሪያ ትምህርት ባለ በፍልስፍና በከንቱም መታለል ማንም እንዳይማርካችሁ ተጠበቁ። (ቆላስይስ 2፡8)*

ጳውሎስ በዚህ ስፍራ፣ የሐሰቱን አስተምህሮ ከንቱ እና አታላይ ፍልስፍና በማለት በቀጥታ ያጋልጠዋል፡፡ እንደተመለከትነው፣ በግሪኩ አጠቃቀም፣ ፍልስፍና የሚለው ቃል የሚያመለክተው፣ በንፁህ አውቀት ወይም ምክንያታዊ በሆነ ጥናት ላይ የተመሰረተውን ሳይሆን በትውፊታዊ ሃይማኖታዊ ምርምሮች ላይ የተመሠረተውን ነው፡፡

በቆላስይስ የነበሩ የሐሰት መምህራን በግሪክ ሃይማኖትና በባዕድ ምሥጢራዊ ሃይማኖት ፍቅር የተነደፉ መሆኑን እነዚህ ቁጥሮች በብርቱ ያመለክቱናል፡፡ በቤተክርስቲያን ውስጥ ተቀባይነትን ለማግኘት፣ ጥቂት ክርስቲያናዊ ልምዶችን አካትተው ሊሆን ይችላል፡፡ ሆኖም ግን ክርስትናን ሐዋርያት እንደሚያስተምሩት አልተቀበሉትም፣ ቢቀበሉትማ ልምዶቻቸውን በትውፊታዊ የባዕድ አምልኮ ላይ ባልመሠረቱት ነበር፡፡

በቆላስይስ ይኖሩ በነበሩ የሐሰት መምህራን ይለፈፍ የነበረው የአህዛብ ፍልስፍና የብህትውናን አንዳንድ ነገሮች ያካተተ ይመስላል፡፡ ብህትውና ምድራዊ ደስታን አግባብ ባልሆነ መንገድ አሻፈረኝ የማለት ልምምድ ነው፡፡ አንዳንድ ጊዜም ጉዳዩን ያለ ልክ በማክረር ደስታ ኢ-ግብረገብ ነው በማለት፣ ከዚህም አልፎ አንድ ሰው አካሉን በማሰቃየት ጽድቁን ሊያሳይ ይገባል ወደማለት ይዘልቃል፡፡ ጳውሎስም ይህንን የመሰለውን የብህትውና አስተሳሰብ በቆላስይስ ምዕራፍ 2 ከቁጥር 20 እስከ 23 እንዲህ ውድቅ ያደርገዋል፡

*ከዓለማዊ ከመጀመሪያ ትምህርት ርቃችሁ ከክርስቶስ ጋር ከሞታችሁ፥*
*እንደ ሰው ሥርዓትና ትምህርት። አትያዝ፥ አትቅመስ፥ አትንካ ለሚሉት ትእዛዛት በዓለም*
*እንደምትኖሩ ስለ ምን ትገዛላችሁ? እነዚህ ሁሉ በመደረግ ሊጠፉ ተወስነዋልና።*

© 2010 by Third Millennium Ministries
www.thirdmill.org

*ይህ እንደ ገዛ ፈቃድህ በማምለክና በትሕትና ሥጋንም በመጨቆን ጥበብ ያለው ይመስላል፥ ነገር ግን ሥጋ ያለ ልክ እንዳይጠግብ ለመከልከል ምንም አይጠቅምም። (ቆላስይስ 2፡20-23)*

ጳውሎስ በቆላስይስ የነበረውን የብህትውና ልምምድ የተቃወመው ቢያንስ በሁለት ምክንያቶች ነው፡፡ አንደኛ፣ ብህትውናቸው የተመሰረተው በዚህ ዓለም መሠረታዊ መርሆች ላይ ነበር፡፡ በዚህ ወደ ኋላ ላይ እንደምንመለከተው፣ ይህ ቋንቋ ከመንፈሳዊ ኃይላትና ከመላእክት ጋር የተሳሰረ ነው፡፡ ሁለተኛ፣ ኃጢአትን ለማሸነፍ የሚያስችል ምንም ፋይዳ የለውም ስለዚህ ምንም ጥቅም የሌለው ከንቱ ነው፡፡

ስናጠቃልለው፣ በቆላስይስ የነበሩት የሐሰት መምህራን የቤተክርስቲያንን አስተምህሮ ከግሪክ ትውፊት ጋር ለመቀየጥ ሞከሩ ይህንንም ያደርጉ የነበረው አማኞች የሚገጥማቸውን ፈተና ለመቋቋም የሚያስችላቸውን እውቀትና ጥበብ ለማግኘት በሚል ሰበብ ነበር፡፡ ወደ እውነቱ ስንመጣ ግን፣ አለን የሚሉት ጥበብ ግን ውሸት ነበር፣ ልምምዶቻቸውም እርባና ቢስ ነበሩ፣ ትምህርቶቻቸውም የክርስቶስን የበላይነት የሚክዱ ናቸው፡፡

በቆላስይስ ይኖሩ የነበሩት የሐሰት መምህራን የግሪክን ፍልስፍና ከማስፋፋታቸው ባሻገር፣ በአይሁድ ህግ ላይ የተመሠረቱ በርካታ ልምምዶችንም ቀይጠው ነበር፡፡ ሆኖም፣ ስለ አይሁድ ህግ ያላቸው ግንዛቤና አጠቃቀማቸው ከትውፊታዊው የጁዳይዝም ሥርዓትም ሆነ ከትክክለኛው የክርስትና ልምምዶች የተገነጠለ ነበር፡፡

**የአይሁድ ህግ**

በሌሎች ትምህርቶች እንዳየነው፣ ጳውሎስ ለሙሴ ህግ ከበሬታ አለው፡፡ ስለወንጌልም ሲል በርካታ ትውፊታዊ የአይሁድ ልምምዶችን ለመቀበልና ለመፈጸም ፈቃደኛ ነበር፡፡ እንግዲያው፣ በቆላስይስ ይኖሩ የነበሩ የሐሰት መምህራን ህጉን አግባብ በሆነ መንገድ ተለማምደው ቢሆን ኖሮ፣ ጳውሎስ ስለ አጠቃቀማቸው ባልነቀፋቸው ነበር፡፡ የእርሱ ነቀፋ የሚያመለክተን የሐሰት መምህራኑ የአይሁድን አስተምህሮና ልምምዶች ይገለገሉባቸው የነበሩት በረከሰ መንገድ ነበር፡፡

በቆላስይስ ምዕራፍ 2 ቁጥር 16 ውስጥ፣ የሐሰት አስተማሪዎች ያበለሻሹዋቸውን የአይሁድ ልምምዶች ጠቃቅሷል፡

*እንግዲህ በመብል ወይም በመጠጥ ወይም ስለ በዓል ወይም ስለ ወር መባቻ ወይም ስለ ሰንበት ማንም አይፍረድባችሁ፤ (ቆላስይስ 2፡16)*

በግልጽ እንደምናስተውለው፣ በቆላስይስ ይኖሩ የነበሩ የሐሰት መምህራን በብሉይ ኪዳን ከተሰጡት ልምምዶች አንዳንዶቹን ያከርሩ ነበር፡፡ ይህም በአይሁድ የቀን አቆጣጠር ውስጥ የተመዘገቡትን በዓላቶች፣ ማለትም ሃይማኖታዊ በዓላትን፣ ጨረቃ አዲስ ስትወጣ የሚከበረውን በዓልና የሰንበትን ቀን በተጨማሪም ከቅባት ነክ ምግቦች መታቀብን ያካትቱ ነበር፡፡ ሆኖም የብሉ ኪዳኑን ሥርዓቶች ያከብሩ የነበረው በሙሴ ህግ ውስጥ በተቀመጠው ዓይነት አልነበረም፡፡ ወይም ደግሞ ሐዋርያት ይለማመዱ ቸንደነበረው ዓይነትም አልነበረም፡፡ ይልቁኑ በተቃራኒው፣ ከአይሁድ ህግ በሚጣረስ መንገድና የተቀታዮቻቸውንም የመጨረሻ ዕጣ ፈንታ አደጋ ውስጥ በሚጥል መንገድ እንደሚለማመዱ ጳውሎስ በገሃድ አጋልጦል፡፡ ይህንንም በቆላስይስ ምዕራፍ 2 ቁጥር 17 እና 18 ውስጥ እንዲህ አስቀምጦታል፡

© 2010 by Third Millennium Ministries
www.thirdmill.org

*እነዚህ ሊመጡ ያሉት ነገሮች ጥላ ናቸውና፥ አካሉ ግን የክርስቶስ ነው።*
*ትሕትናንና የመላእክትን አምልኮ እየወደደ፥ ባላየውም ያለ ፈቃድ እየገባ፥ በሥጋዊም አእምሮ በከንቱ እየታበየ ማንም አይፍረድባችሁ። (ቆላስይስ 2፡17-18)*

የሙሴ ህግ የተቀደሱ ቀናትን እግዚአብሔርን ከማምለክ ጋር እንጂ ከመላእክት አምልኮ ጋር አላቆራኘውም፡፡ ምግብ መርጦ መመገብን ለእግዚአብሔር እንደተለየ ህዝብ መለያቸው እንዲሆን እንጂ የትህትና መገለጫና የብህትውና መንገድ አድርጎም ጥብቅና አልቆመለትም፡፡ የሐሰት መምህራን ግን፣ እነዚህን ህግጋት በመበረዝ፣ ለጣዖት አምልኮና ለአህዛብ ብህትውና ይጠቀሙባቸው ነበር፡፡

በቆላስይስ ምዕራፍ 2 ቁጥር 11 እና 12 ውስጥ፣ ጳውሎስ በተጨማሪም የስህተት አስተማሪዎች በርዘው የሚጠቀሙበትን የአይሁድን የመገረዝ ህግ በዝርዝሩ ውስጥ ያካትተዋል፡፡

*የሥጋንም ሰውነት በመገፈፍ፥ በክርስቶስ መገረዝ፥ በእጅ ባልተደረገ መገረዝ በእርሱ ሆናችሁ ደግሞ ተገረዛችሁ፤*
*በጥምቀትም ከእርሱ ጋር ተቀብራችሁ፥ በጥምቀት ደግሞ፥ ከሙታን ባስነሣው በእግዚአብሔር አሠራር በማመናችሁ፥ ከእርሱ ጋር ተነሣችሁ። (ቆላስይስ 2፡11-12)*

በግልጽ እንደምናየው፣ በቆላስይስ የሚኖሩ የሐሰት መምህራን የክርስትናን ግርዘት የሚመስል ልምምድ ያራምዳሉ፡፡ ስለዚህ፣ ጳውሎስ ግርዘትንና የክርስትና ጥምቀትን አያይዞ የተናገረው የቆላስይስ ሰዎች ስለተጠመቁ ግርዘት እንደማያስፈልጋቸው ሊስተምራቸው ነው፡፡

በአጭሩ፣ በቆላስይስ መልእክቱ ጳውሎስ የጻፈው ህጉን የሚሸቃቅጡትን ለመቃወም ብሎ እንጂ ህጉን ራሱን ለመቃወም ብሎ አልነበረም፡፡ በሌላ ስፍራ፣ የሙሴ ህግ ለትክክለኛው ክርስቲያናዊ ግብረገብነትና ልምምድ መሠረት እንደሆነ እና ስለ እግዚአብሔርም ብዙ እውነቶችን እንደሚያስተምረን ጳውሎሰ ማረጋገጫ ሰጥቷል፡፡ በዚህ በቆላስይስ ግን፣ በተመረጡ የስህተት አስተምህሮዎችና ልምምዶች ላይ በማነጣጠር የሚፋለማቸው ሲሆን፣ በህጉ ውስጥ ያሉ አንዳንድ ትዕዛዛትን በመሸቃቀጣቸው ይረግማቸዋል ቤተክርስቲያንም እነዚህን የተሸቃቀጡ ልምምዶች እንዳትቀበል ያሳስባል፡፡

በቆላስይስ የሚኖሩ የሐሰት መምህራን የግሪክን ፍልስፍና ከማራመዳቸው እና በአይሁድ ህግ ላይ የተመሠረቱ ልምምዶችን ከመቀየጣቸው ባሻገር፣ የመናፍስትን አምልኮ በመስበክ ክርስቲያኖች እነዚህን ኃይላት እንዲያከብሩና እንዲያመልኩ ያበረታታሉ፡፡

**መንፈሳዊ ኃይላት**

እንግዲህ የቆላስይስ ቤተክርስቲያን መንፈሳዊ ኃይላትን የማምለክ ልምምድ የነበራት መሆኑ ቢያንስ በሦስት መንገዶች በግልፅ ይታያል፡፡ አንደኛ፣ ጳውሎስ ስለ መላእክት አምልኮ ጽፏል፡፡ ሁለተኛ፣ ስለ ኃይላትና ሥልጣናት ጠቅሷል፡፡ ሦስተኛ ደግሞ፣ ከዚህ ዓለም መሠረታዊ መርሆዎች ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ችግሮች ጠቅሷል፡፡ ስለ መላእክት አምልኮ የተቀሰውን በመመልከት እንጀምር፡፡

እንደ መጽሐፍ ቅዱስ አገላለጽ፣ መላእክት የእግዚአብሔር አገልጋዮች ናቸው፡፡ በፍጥረት ውስጥ ከእግዚአብሔር እየተቀበሉ የሚፈፅሙት ተግባር አላቸው፡፡ እግዚአብሔር በርካታ ሥራዎችን ሰጥቷቸዋል፣ መንፈሳዊ ውጊያን፣

© 2010 by Third Millennium Ministries
www.thirdmill.org

በብሔራዊ ፖለቲካ ላይ ተፅዕኖ ማሳደርን፣ ለህዝቡ መልእክትን ማድረስን እና አማኞች በምድር ኑሯቸው የሚስፈልጓቸውን በማዘጋጀት ያገለግላሉ፡፡ የመጀመሪያዪቱም ቤተክርስቲያን እነዚህን ኃላፊነቶቻቸውን በደንብ ታውቃለች፡፡ በዕብራውያን ምዕራፍ 1 ቁጥር 14 እንዲህ ይነበባል፡

*ሁሉ መዳንን ይወርሱ ዘንድ ስላላቸው ለማገዝ የሚላኩ የሚያገለግሉም መናፍስት አይደሉምን? (ዕብራውያን 1፡14)*

መላእክት በእርግጥ አገልጋይ መናፍስት ናቸው፣ እናም ሥራቸውን መለየት በጣም ወሳኝ ነው፡፡ በቆላስይስ እንደነበሩት የሐሰት መምህራን ግን፣ መላእክት ከአገልጋይነት የዘለሉ ናቸው፤ ለሚያመልኩዋቸውና ትእዛዛቶቻቸውን ለሚጠብቁ ምሥጢራዊ እውቀቶችን የሚገልጡ ፈለካዊ ኃይላት ናቸው፡፡ ጳውሎስ በቆላስይስ ምዕራፍ 2 ቁጥር 18 ውስጥ እንዲህ ሲል በቀጥታ ኮንኗቸዋል፡

*ትሕትናንና የመላእክትን አምልኮ እየወደደ፥ ባላየውም ያለ ፈቃድ እየገባ፥ በሥጋዊም አእምሮ በከንቱ እየታበየ ማንም አይፍረድባችሁ። (ቆላስይስ 2፡18 )*

የሐሰት መምህራኑ ከመላእክት ራእይ ተቀብለናል ይላሉ፣ እናም ክርስቲያኖችም ተገቢ የሆነውን የባዕድ አምልኮ ሥርዓት ቢፈፅሙ ተመሳሳይ ራእይ እነርሱም ሊቀበሉ ይችላሉ በማለት ያባብላሉ፡፡

ምናልባት የሐሰት መምህራኑ ራእይ ተቀብለው ሊሆን ይችላል፣ ሆኖም ይህ ራእይ ከእግዚአብሔር ቅዱሳን መላእክት ሳይሆን ከአጋንንቶች ነው፡፡ ሌላኛው አማራጭ ደግሞ፣ ምናብ ወለድ የራስ ቅዠት ወይም የአደገኛ ዕፆች ሱስ የወለደው ባዶ የቁም ቅዠት ሊሆን መቻሉ ነው፡፡ ወይም ደግሞ እየዋሹም ሊሆን ይችላል፡፡

ምንም ይሁን ምን፣ በጥንታዊው ዓለም ውስጥ ይህንን የመሰለው የመላእክትን ኃይልና ተፅዕኖ ፈጣሪነት አጋንኖ የመመልከት አስተሳሰብ እንግዳ አልነበረም፡፡ አንዳይድ የአይሁድ መምህራንም ስለመላእክት ተመሳሳይ የሆነ አስተሳሰብ ያራምዳሉ፡፡ አንዳንድ የግሪክ ፈላስፎችም ስለ አማልክቶቻቸውን ስለ ኮከቦቻቸው ተመሳሳይ ነገሮችን ያስተምራሉ፡፡ የሚያሳዝነው፣ በእነዚህ ሃሳቦች መካከል ያለው መመሳሰል የቆላስይስ ክርስቲያኖች የሐሰት መምህራኑን አስተምህሮ ትክክለኛ ነው ብለው እንዲያስቡና ይህ የስህተት አስተምህሮ በቆላስይስ ቤተክርስቲያን ውስጥ መቆናጠጫ እንዲያገኝ እንዲፈቅዱለት አድርጎታል፡፡

ጳውሎስ ስለ መላእክት አምልኮ በቀጥታ የጠቀሰውን እስካሁን ተመልክተናል፣ አሁን ደግሞ ስለ ኃይላትና ስለ ሥልጣናት ወደተናገረው መለስ እንበል፡፡ በመጀመሪያው ክፍለ ዘመን ቋንቋ ውስጥ፣ “ኃይላት” እና “ሥልጣናት” የሚለው ቃል መላእክትን ለመሳሰሉ መንፈሳዊ ፍጥረታት አገልግሎት ላይ ይውላል፡፡

እንደተመለከትነው፣ በቆላስይስ ይኖሩ የነበሩ የሐሰት መምህራን አማኞች መላእክትንና መንፈሳዊ ፍጥረታትን እንዲያመልኩ ያበረታታሉ፡፡ ጳውሎስ ለዚህ የስህተት አስተምህሮ ምላሽ የሰጠው በሰማይም ሆነ በምድር ከሚገኙት ኃላትና ሥልጣናት ሁሉ ክርስቶስ እጅግ የሚልቅ መሆኑን በአፅንዖት በመግለጥ ነው፡፡ በቆላስይስ ምዕራፍ 1 ቁጥር 16 ውስጥ ስለ ክርስቶስ ልዕልና እንዲህ ጽፏል፡

*የሚታዩትና የማይታዩትም፥ ዙፋናት ቢሆኑ ወይም ጌትነት ወይም አለቅነት ወይም ሥልጣናት፥ በሰማይና በምድር ያሉት ሁሉ በእርሱ ተፈጥረዋልና ከፍጥረት ሁሉ በፊት በዟር ነው፤ ሁሉ በእርሱና ለእርሱ ተፈጥሮአል፤ (ቆላስይስ 1፡16)*

© 2010 by Third Millennium Ministries
www.thirdmill.org

ጳውሎስ በዚህ ስፍራ ዙፋናትን፣ ኃይላትን፣ ጌትነትንና ሥልጣናትን ጠቅሷል፡፡ ዙፋናትና ኃይላት ትርጓሜያቸውን ያገኙት *thronos* (qro,noj) እና *kuriotēs* (kurio,thj) ከተሰኙት የግሪክ ቃላት ነው፡፡ እነዚህ ቃላት በተለምዶ የሚጠቀሱት ምድራዊ ነገሥታትንና ገዢዎችን ለማመልከት ሲሆን፣ መንፈሳዊ ፍጥረታትን ለማመልከትም ይጠቀሙባቸዋል፡፡ ገዢዎችና ሥልጣናት ደግሞ ትርጓሜያቸውን ያገኙት *archē* (avrch,) እና *exousia* (evxousi,a) ከተሰኙት የግሪክ ቃላት ነው፡፡ እነዚህ ቃላት አብዛኛውን ጊዜ በጥቅም ላይ የሚውሉት የማይታዩ ኃይላትን ማለትም መላእክትንና አጋንንትን ለመጥቀስ ነው፡፡

በቆላስይ ይገኙ በነበሩት የሐሰት መምህራን ንፅረተ-ዓለም ውስጥ፣ የመላእክትና የአጋንንት መንፈሳዊ ሥልጣናት በምድር ከሚገኙ ሰብዓዊ አቻ ፍጡራን እጅግ ይበልጣሉ የሚል ድምዳሜ አለ፡፡ የሐሰት መምህራኑ የመላእክትንና የአጋንንትን ኃይል ያለ ልክ ያጋንናሉ፡፡ ከዚህም የተነሳ ለክርስቶስ ብቻ ይገባው የነበረውን የማንነት መገለጫ ለእነዚህ ለማይታዩ ገዢ ኃይላት ለአለቆችና ሥልጣናት ሰጥተው ነበር፡፡

ጳውሎስ ስህተታቸውን ያሳየው ክርስቶስ የፍጥረታት ሁሉ ጌታ በማለት እያወደሰ ነው፡፡ ጳውሎስ በመንፈሳዊ እና በምድራዊ ባለሥልጣናት መካከል ያለውን ልዩነት ከማሳየት ይልቅ፣ አንድ ናቸው፣ ከልዩነታቸው ይልቅ ተመሳሳይነታቸው ይጎላል በማለት አመልክቷል፡፡ ሁሉም ተፈጥረዋል፣ ሁሉም ከክርስቶስ በታች ናቸው፡፡ እውነተኛው ንጽጽር የሚታየው የሐሰት መምህራን እንደሚያራግቡት መንፈሳዊና ምድራዊ በማለት ሳይሆን ክርስቶስ የሁሉ የበላይ ከመሆኑ ጋር ነው፡፡ በቆላስይስ ምዕራፍ 1 ቁጥር 16 የጠቀሰውን ደግመን እንመልከተው፡

> *በሰማይና በምድር ያሉት ሁሉ በእርሱ ተፈጥረዋልና (ቆላስይስ 1፡16)*

ጳውሎስ በመቀጠልም መንፈሳዊ ኃይላትና ክርስቶስ ቀጥተኛ ፍልሚያ ውስጥ እንደነበሩ በግልጽ ተናግሯል፡፡ የሐሰት መምህራኑ የሚያስተምሩት ክርስቶስን ማምለክ መንፈሳዊ ሥልጣናትን ከማምለክ ጋር ይስማማል ብለው ነው፡፡ ጳውሎ ግን የሐሰት አስተማሪዎች የሚያመልኩዋቸውን መንፈሳዊ ፍጥረታት በምንም ዓይነት መንገድ ይመልከቷቸው በምንም፣ አውነቱ ግን አምልኮን የሚጠየቁት አጋንንቶች ናቸው በማለት ያጋልጣል፡፡ የእግዚአብሔር ቅዱሳን መላእክት ይህንን ከመሰለው አምልኮተ ጣዖት ጋር ግንኙነት የላቸውም፡፡ ክርስቶስን የጠላቶቹን መመለክ ፈጽሞ አይፈቅድም፡፡

ጳውሎስ ይህንን ነጥብ በቆላስይስ ምእራፍ 2 ቁጥር 15 ውስጥ አብራርቶታል፡

> *አለቅነትንና ሥልጣናትን ገፎ፥ ድል በመንሣት በእርሱ እያዞራቸው በግልጥ አሳያቸው።*
> *(ቆላስይስ 2፡15 )*

እግዚአብሔር በኢየሱስ ክርስቶስ መስቀል አማካይነት መንፈሳዊ ኃይላትን እና ሥልጣናትን ድል አድርጎ አለቅነታቸውን ገፏል፡፡ በሌላ አገላለጽ፣ መንፈሳዊ ኃይላትና ሥልጣናት በመንፈሳዊ ውጊያ የእግዚአብሔር ተቃዋሚ መሆናቸውን ያገለፃሉ፡፡ አምፀዋል፣ ክፉ መናፍስት ናቸው፣ ደግሞም የእግዚአብሔር ጠላቶች ናቸው፡፡ እነርሱ አጋንንቶች እንጂ፣ ቅዱሳት መላእክት አይደሉም፡፡ እግዚአብሔር ግን በኢየሱስ ክርስቶስ አማካይነት፣ እነዚያን አጋንንቶች ሥልጣናቸውን ገፏል ድል በማድረግም አዋርዷቸዋል፡፡ እንግዲህ በቆላስይስ ይኖሩ በነበሩ የሐሰት መምህራን ይመለኩ የነበሩት እና ጳውሎስ "ገዢዎችና ሥልጣናት" በማለት የጠቀሳቸው መንፈሳዊ ኃይላት እነዚህ የወደቁ እና የተሸነፉ አጋንንቶች ናቸው፡፡

ጳውሎስ ስለ መላእክት፣ ስለ መንፈሳዊ አለቆችና ሥልጣናት የተናገረውን ከመረመርን፣ አሁን ደግሞ ጳውሎስ ስለዚህ ዓለም መሠረታዊ መመሪያዎች (የመጀመሪያ ትምህርት) እንዴት እንደተናገረ ወደመመልከቱ እንሸጋገራለን፡፡ አስቀድመን እንደተናገርነው፣ ይህኛውም ሐረግ ለመንፈሳዊ ፍጥረታት ይጠቀስ የነበረ ሌላኛው ሐረግ ነው፡፡

በመጀመሪያው ክፍለ ዘመን፣ *stoicheia* (stoicei/a) የተሰኘው የግሪክ ቃል *"መሠረታዊ መመሪያዎች"* ተብሎ ይተረጎማል፡፡ ይህም በተለምዶ ከከዋክብትና ከፕላኔቶች ጋር ለሚያያዙ ጣዖታትና መንፈሳዊ ኃይላት መግለጫ የሚውል ነው፡፡ *stoicheia* በተጨማሪም አራት መሠረታዊ ግዑዛን አካላትን ማለትም፣ መሬትን፣ ንፋስን፣ እሳትንና ውሃን ለማመልከት ያገለግላል፡፡ እነዚህ መሠረታዊ መርሆች ወይም ግዑዛን ፍጥረታት የወንዶችንና የሴቶችን ዕጣ ፈንታ ይወስናሉ አሊያም ተፅዕኖ ያሳድሩበታል ተብሎ ይታሰባል፡፡

ጳውሎስም በገላትያ ምእራፍ 4 ቁጥር 8 እና 9 ውስጥ *stoicheia* የተሰኘውን ቃል በዚህ መንገድ ተጠቅሞበታል፡

> ***ነገር ግን በዚያን ጊዜ እግዚአብሔርን ሳታውቁ በባሕርያቸው አማልክት ለማይሆኑ ባሪያዎች ሆናችሁ ተገዛችሁ፤***
> ***አሁን ግን እግዚአብሔርን ስታውቁ ይልቅስ በእግዚአብሔር ስትታወቁ እንደ ገና ወደ ደካማ ወደሚናቅም ወደ መጀመሪያ ትምህርት እንዴት ትመለሳላችሁ? እንደ ገና ባሪያዎች ሆናችሁ ዳግመኛ ለዚያ ልትገዙ ትወዳላችሁን? (ገላትያ 4፡8-9)***

በዚህ ስፍራ የመጀሪያ ትምህርት ተብሎ የተጠቀሰው ቃል ትርጓሜውን ያገኘው *stoicheia* ከተሰኘው የግሪክ ቃል ሲሆን፣ የሚያመለክተውም በፍጥረታቸው አማልክት ያልሆኑትን ፍጥረታት ነው፡፡ ያም ማለት፣ ራሳቸውን የአህዛብ አማልክት በሚል ጭንብል የሸፈኑ አጋንንቶችን ያሳያል፡፡ ሌላኛው ጳውሎስ በቆላስይስ ምዕራፍ 2 ቁጥር 8 የጠቀሰውና ይህንን የመጀመሪያ ትምህርት የኮነነበት ቃል የተገኘው ከዚሁ *stoicheia* ከተሰኘው ቃል ነው፡፡

ጳውሎስም ይህንን *stoicheia* ወይም የመጀመሪያ ትምህርት የሚለውን ቃል ያመለከተው የሐሰት መምህራኑ ፍልስፍና መሠረት መሆኑን ለማሳየት ነው፡፡ በሌላ አባባል፣ የሐሰት መምህራኑ ሃይማኖታዊ ትውፊት ተቀባይ ሊያጣ ይገባዋል ምክንያቱም የሚታመኑት በሐሰት አማልክት ላይ ነውና የሚል መከራከሪያ ጳውሎስ ያቀርባል፡፡

ከሁሉ የሚገርመው ደግሞ፣ ስለዚህ ግዑዛንና ስለ መንፈሳዊ ኃይላት የሚናፈሰው አስተሳሰብ በተለይ በሁለቱ ኪዳናት የሽግግር ዘመን ውስጥ በአንዳንድ የጁዳይዝም ክንፎች ውስጥም ይቀነቀን ነበር፡፡ በጳውሎስ ዘመን በነበረችው የቆላስይስ ቤተክርስቲያን ውስጥ ክርስትናን ከተሳሳቱ አስተምህሮዎች ጋር ለመሸቃቀጡ መድረክ ያመቻቸው ይህ ነው ተብሎ ይታሰባል፡፡ በቆላስይስ ይኖሩ የነበሩ የሐሰት መምህራን የአይሁድን ህጎችን፣ የአህዛብን ሃይማኖትና ክርስትናን ያደበላለቁ ሲሆን፣ *የመጀመሪያ ትምህርት stoicheia በመባል በዘልማድ የሚታወቀውን የከዋክብት ኃይላት አምልኮም ያበረታቱ ነበር፡፡*

*በመጀመሪያው ክፍለ ዘመን የነበረችው የቆላስይስ ቤተክርስቲያን ጥቂት ገሃድ ችግሮን ተጋፍጣ ነበር፡፡ ከሌሎቹ አብያተክርስቲያናት ለየት ባለ መንገድ የሐዋርያትን ትምህርቶች አግኝተው አያውቁም፡፡ ምንም እንኳን ቤተክርስቲያኒቱ እግዚአብሔርን በሚወድዱ ሰዎች ብትመሠረትም፣ በጠንካራ የሐዋርያት ነገረ-መለኮት ላይ አልተተከለችም ነበር፡፡ ስለዚህም፣ የሐሰት መምህራኑ በተደበላለቁ የጁዳይዝም እና የጣዖት አምልኮ ትምህርቶች ሲጨናንቋቸው፣ በእውነቱና በስህተቱ መካከል ያለውን ልዩነት መናገር ያስቸግራቸው ነበር፡፡ ብልህነታቸው ግን፣ ችግሮቻቸውን በመረዳት ጳውሎስ እንዲረዳቸው ጥያቄ ማቅረባቸው ነው፡፡*

# 3. አወቃቀርና ይዘት

እስካሁን ድረስ ጳውሎስ ለቆላስይስ ቤተክርስቲያን የጻፈውን ደብዳቤ ዳራ ስንዳስስ ከቆየን፣ አሁን ደግሞ ወደ ቀጣዩ ርዕሳችን፡ ጳውሎስ ለቆላስይስ ቤተክርስቲያን የጻፈውን መልእክት አወቃቀርና ይዘት ወደመመልከቱ እንሸጋገር፡፡

© 2010 by Third Millennium Ministries
www.thirdmill.org

ጳውሎስ ለቆላስይስ ቤተክርስቲያን የጻፈው መልእክት በአራት ዋና ክፍሎች ሊከፈል ይችላል፡ ምዕራፍ 1 ቁጥር 1 እና 2 ሰላምታ፤ በምእራፍ 1 ቁጥር 3 እስከ 14 ምሥጋናና ምልጃ፤ ከምዕራፍ 1 ቁጥር 15 እስከ ምዕራፍ 4 ቁጥር 6 ድረስ ስለ ክርስትና የበላይነት የሚያወሳው የመልእክቱ ዋና አካል እና በመጨረሻም ምዕራፍ 4 ከቁጥር 7 እስከ 18 የስንብት ሰላምታ ይሆናሉ፡፡

## ሰላምታ

በምዕራፍ 1 ቁጥር 1 እና 2 የሚገኘው ሰላምታ፣ ሐዋርያው ጳውሎስ ሥልጣን የጠሰጠው የዚህ መልእክት ጸሐፊ አድርጎ ሲጠቅሰው፣ በተጨማሪም ደብዳቤው ከጳውሎስ ደቀመዝሙር ከጢሞቴዎስም እንደመጣ ይጠቅሳል፡፡ የመልእክቱ ተቀዳሚ ጸሐፊ ጳውሎ እንደሆነ እናውቃለን ምክንያቱም በመልእክቱ ላይ ፊርማውን ያሳረፈው ጳውሎስ ብቻ ነው፡፡ በተጨማሪም በሰላምታው ውስጥ የሰላምታው አካል ሆኖ አጭር የበረከት ቃልም ተካቷል፡፡

## ማበረታቻዎች

ምሥጋናንና ምልጃን ያካተቱት የማበረታቻ ቃሎች የሚገኙት በምእራፍ 1 ከቁጥር 3 እስከ 14 ውስጥ ሲሆን፣ ጳውሎስ ስለ ቆላስይስ ቤተክርስቲያን ከኤጳፍራ የተቀበለው ሪፖርት ተያይዞ ይቀርባል፡፡ ኤጳፍራ በቆላስይስ የምትገኘውን ቤተክርስቲያን የመሠረተ አገልጋይ ነው፡፡ በተጨማሪም ጳውሎስ በእስር ላይ በነበረበት ወቅት አብሮት እንደነበር ትዝ ይላችኋል፡፡ ጳውሎስን ሲጎበኝ፣ በቆላስይስ ስለነበሩ አማኞች ፍቅርና እምነት ደግሞም ለቆላስይስ ቤተክርስቲያን አብዛኛውን ጊዜያቸውን በጸሎት ስለሚጋደሉ ሁለት ሰዎች ኤጳፍራ ለሐዋርያው እና ይነግረዋል፡፡ ስለዚህም፣ ጳውሎ ሲጽፍላቸው፣ ስለ መዳናቸውና ስለ እምነታቸው እንዴት እግዚአብሔር ዘወትር እንደሚያመሰግን ይነግራቸዋል፡፡ ደግሞም ጌታ የመለየትን መንፈሳዊ እውቀት በመስጠት ለመልካም ሥራ ሁሉ የተዘጋጁ እንዲሆኑ እንዲባርካቸው አዘውትሮ የሚጸልይላቸው መሆኑንም ይነግራቸዋል፡፡

## የመጨረሻ ሰላምታ

በቆላስይስ መጽሐፍ የመጨረሻ ክፍል፣ ማለትም በምዕራፍ 4 ከቁጥር 7 እስከ 18 በሚገኘው የስንብት ሰላምታ፣ በታሰረበት ስፍራ ከጳውሎስ ጋር ከነበሩ የቆላስይስ ሰዎች ለቤተክርስቲያኒቱ የተላከውን ሰላምታ ጳውሎስ ያቀርባል፡፡ መደምደሚያው እንደሚያመለክተው ጳውሎስ ደብዳቤውን የላከው በቲኪቆስና በአናሲሞስ እጅ ነው፡፡ ቲኪቆስ በተጨማሪም ለኤፌሶን የተጻፈውን ደብዳቤ ያደረሰ ሲሆን፣ አናሲሞስ ደግሞ ለፊልሞና የተጻፈውን አድርሷል፡፡ ይህም የቆላስይስ፣ የኤፌሶንና የፊልሞና ደብዳቤዎች በተመሳሳይ ጊዜ የተጻፉና የተላኩ ሊሆኑ እንደሚችሉ ያመለክተናል፡፡

ጳውሎስ በመዝጊያው ላይ ለሎዶቅያ ቤተክርስቲያን ስለ ጻፈው ደብዳቤም ይጠቅስና የቆላስይስ ሰዎች እንዲያነብቡት፣ ለእነርሱ የጻፈውንም ለሎዶቅያ እንዲያስነብቡ ያዝዛቸዋል፡፡ ምንም እንኳን ጳውሎስ መልእክቶቹን የጻፈው በአንድ ሁኔታ ውስጥ ለነበሩ ውሱን ሰዎች ቢሆንም፣ ለተለያዩ ተደራሲያንም አገልግሎት ሊሰጥ እንደሚችል ከዚህ መረዳት እንችላለን፡፡ ወደኋላ ላይ በምንመለከታቸው ትምህርቶች እንደምናየው፣ ጳውሎስ ለሎዶቅያ ሰዎች የተጻፈ ደብዳቤ ተብሎ የተጠቀሰው መልእክት ሊሆን የሚችለው የኤፌሶን መልእክት ነው፡፡

© 2010 by Third Millennium Ministries
www.thirdmill.org

# የክርስትና የበላይነት

ጳውሎስ ለቆላስይስ ሰዎች የጻፈው ደብዳቤ ዋና አካል የሚጀምረው በምዕራፍ 1 ቁጥር 15 ሲሆን፣ እስከ ምዕራፍ 4 ቁጥር 6 ይዘልቃል፡፡ ይህ ክፍል የሐሰት መምህራን ከሚያራምዷቸው ሃይማኖቶች ሁሉ ክርስትና ይበልጣል የሚለውን ነጥብ ያጎላል፡፡

ጳውሎስ ስለ ክርስትና የበላይነት ያነሳው ሃሳብ በግርድፉ በአራት ዋና ክፍሎች ይከፈላል፡ አንደኛ፣ በምዕራፍ 1 ከቁጥር 15 እስከ 20 የጠቀሰው የክርስቶስ የበላይነት ነው፡፡ ሁለተኛ፣ በምዕራፍ 1 ከቁጥር 21 እስከ እስከ ምዕራፍ 2 ቁጥር 5 የተጠቀሰው የክርስቶስ አገልጋዮች የበላይነት ነው፡፡ ሦስተኛ፣ በምዕራፍ 2 ከቁጥር 6 እስከ እስከ 23 የሚገኘው በክርስቶስ ያገኘነው መዳን የበላይነት ነው፡፡ አራተኛ ደግሞ፣ በምዕራፍ 3 ቁጥር 1 እስከ ምዕራፍ 4 ቁጥር 6 የተጠቀሰው የክርስቲያናዊ አኗኗር የበላይነት ነው፡፡ በክርስቶስ የበላይነት ላይ ከሚያተኩረው ከመጀመሪያው ክፍል በመጀመር፣ እያንዳንዳቸውን ክፍሎች እንዳስሳቸዋለን፡፡

## የክርስቶስ የበላይነት

የቆላስይስ ቤተክርስቲያን ፈለካዊ መንፈሳዊ ኃይላትን እንድታመልክ የሐሰት መምህራን ሊያግባቧቸው ይጥሩ ነበር፡፡ የብህትውናን የአኗኗር ዘይቤ እንዲከተሉ ያበረታታሉ፣ ይህንንም የሚያደርጉት ይህንን የመሰለው የጉስቁልና ኑሮ መንፈሳዊ ኃይላትን ያባብላል፣ ከሐሰት አማልክትም ብዙ ጥቅሞችን ያስገኛል ብለው ያስቡ ነበር፡፡ ስለዚህም፣ ይህንን የስህተት አስተምህሮ መጋፈጥ የሚጀምረው አማልክት ናቸው ከተባሉት ሁሉ ክርስቶስ የበላይ ነው በማለት ነው፡፡

በአንድ በኩል፣ ክርስቶስ የፍጥረት ንጉሥ ነው ስለዚህም ሁሉ በእርሱ ቁጥትርና ሥልጣን ስር ነው በማለት ጳውሎስ ይሟገታል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ፣ የዚህ ዓለም የመጀመሪያ ትምህርት የተባሉት ደግሞ የድነትን በረከት ሊያስገኙ ስለማይችሉ ከበሬታ የሚገባቸው አይደሉም በማለት ጳውሎስ ያስተምራል፡፡

ጳውሎስ በቆላስይስ ምዕራፍ 1 ከቁጥር 15 እስከ 20 ድረስ ስለ ክርስቶስ የበላይነት በርካታ ወሳኝ ገጽታዎችን ይጠቃቅሳል፡፡

ጳውሎስ የሚጀምረው ክርስቶስ የማይታየው አምላክ ምሳሌ ነው በማለት ነው፡፡ ይህ መግለጫ ክርስቶስን የሚገልፀው የሐሰት መምህራኑን አማልክት ራቁታቸውን በሚያስቀር መንገድ ነው፡፡ ጳውሎስ በቆላስይስ ምዕራፍ 1 ቁጥር 15 እና 16 ውስጥ ኢየሱስን እንዴት እንደገለፀው አድምጡ፡

> ***እርሱም የማይታይ አምላክ ምሳሌ ነው፤ የሚታዩትና የማይታዩትም፥ … በሰማይና በምድር ያሉት ሁሉ በእርሱ ተፈጥረዋልና ከፍጥረት ሁሉ በፊት በኲር ነው፤ ሁሉ በእርሱና ለእርሱ ተፈጥሮአል፤ (ቆላስይስ 1፡15-16)***

ምንም እንኳን ቅዱሳት መጻሕፍት የሰው ዘርን በጠቅላላ እንደ እግዚአብሔር አምሳል አድርገው ብዙ ጊዜ ቢጠቅሱም፣ ጳውሎስ ግን በዚህ ስፍራ ስለ ኢሱስ አንድ ለየት ያለ ነገር በልቡናው ይዟል፣ ይህም በፍጥረት ላይ ካለው ኃይልና ሥልጣን ጋር ተያያዥነት ያለው ነው፡፡ በቆላስይስ ይኖሩ የነበሩ የሐሰት መምህራን “የእግዚአብሔር አምሳል” የሚለውን መግለጫ ከግሪክ ፍልስፍና ተውሰው የሚጠቀሙበትን አጠቃቀም በልቡናው ይዞ ነበር፡፡

© 2010 by Third Millennium Ministries
www.thirdmill.org

በጳውሎስ ዘመን ከነበሩ የግሪክ ፍልስፍናዎች በጥቂቶቹ፣ ፍጥረተ ዓለም እንደ እግዚአብሔር አምሳል ይቆጠር ነበር፣ ማለትም ፍጥረት የእግዚአብሔር ትልቅ መገለጥ ነው፣ አንድም ሰው እውቀትንና ጥበብን የሚያገኘው በፍጥረት መገለጥ አማካይነት ነው ማለት ነው:: የዚህን ሃሳብ ማጣቀሻ የምናገኘው ከጥንት ከአራተኛው ዓ.ዓ. ጀምሮ በነበረው ጢሜዎስ (*Timaeus*) ከተሰኘው የፕላቶ ጽሁፍ ጀምሮ ሲሆን፣ በሁለተኛውና በሦስተኛው ዓ.ም. በነበረውና god Thrice Great Hermes በተሰኘው የኖስቲሳውያን ጽሁፍ ውስጥ ነው::

ስለዚህ፣ የሐሰት መምህራኑ ፕላኔቶችንና ግዑዛን ፍጥረታትን እንደ እግዚአብሔር አምሳል ሲመለከቱ፣ ጳውሎስ የእግዚአብሔር አምሳል ክርስቶስ ነው በማለት ወደ ክርስቶስ ያመለክታል:: "የእግዚአብሔር አምሳል" የሚለውን የዚህን የግሪክ ፍልስፍና መግለጫ በመዋስ፣ አምሳሉ በሐሰት መምህራኑ የሚመለኩት ኢጋንንቶች ሳይሆኑ የእግዚአብሔር ወደር የለሽ አምሳል ክርስቶስ ነው፣ አማኞችም የእግዚአብሔርን የላቀ ጥበብና እውቀት ለማግኘት ሊመለከቱ የሚገባቸውም ወደ እርሱ ነው ይላል::

ጳውሎስ በሁለተኛ ደረጃ የሚጠቅሰው፣ ክርስቶስ የፍጥረት ሁሉ በኵር ነው በማለት ነው:: ጳውሎስ የሐሰት መምህራኑን ለመሞገት ቃላቶቹን በጥንቃቄ ይመርጣል:: በቆላስይስ ምዕራፍ 1 ቁጥር 15 እና 16 ስለ ክርስቶስ የጻፈውን እንደገና አድምጡ፡

> ***እርሱም የማይታይ አምላክ ምሳሌ ነው፤ ... ከፍጥረት ሁሉ በፊት በኵር ነው፤ ሁሉ በእርሱና ለእርሱ ተፈጥሮአል፤ (ቆላስይስ 1፡15-16)***

በዚህ ስፍራ "ከፍጥረት ሁሉ በፊት በኵር ነው" ተብሎ የተተረጎመው *prōtotokos* (prwto,tokoj) የተሰኘው የግሪክ ቃል ሲሆን በተደጋጋሚ የሚያመለክተውም ከመወለድ ቅድሚ ይልቅ የበላይነትንና ሥልጣንን ነው::

በጥንታዊው ዓለም፣ በአንድ ቤተሰብ ውስጥ ብኵርና የሚሰጠው ልጅ የግድ መጀመሪያ የተወለደው አይሆንም:: ይልቁኑ በኵር የሚባለው ከወላጆቹ ውርስ አብዛኛውን ክፍል የሚወስደው ነው:: በተለይም ይህ ልጅ አባትየው ሲሞት ቤተሰቡን የመምራት ሃላፊነት የሚወስድ ልጅ ነው:: ለምሳሌ፣ ከወንዶቹ ልጆች ትልቅየው ምንም እንኳን ታላቅ እህት ብትኖረውም እንደ በኵር ይቆጠራል:: ከዚህም ባሻገር፣ ከሁሉ ታላቅ ሆኖ የተወለደው ልጅ በአንድ ምክንያት ያንን ክብር ካጣ ታናሽየው እንደ በኵር ይቆጠራል::

እንግዲህ አሁን፣ ገናና የሆኑት የሐሰት እምነቶች "በኵር" የተሰኘውን ቃል እንዴት በተሳሳተ መንገድ እንደተረዱትና ክርስቶስ ዓለም ከመፈጠሯ አስቀድሞ "እንደተወለደ" የመቁጠራቸውን ስህተት እንመልከት:: ያም፣ ክርስቶስ ፍጡር እንደሆነ ማመናቸው ሲሆን፣ ከዚህም የተነሣ፣ ከእግዚአብሔር አብ ጋር በኃይልና በሥልጣን እኩል አይደለም ማለታቸው ነው:: ጳውሎስ ግን የክርስቶስን "ብኵርና" ያገናኘው ከፍጥረታት ሁሉ እጅግ የበላይ ከመሆኑና ከሥልጣኑ ጋር ሲሆን፣ አንድም ስፍራ ኢየሱስ ያልነበረበት ዘመን እንደነበር አላመለከተም::

ጳውሎስ ክርስቶስ የፍጥረት ሁሉ በፊት በኵር ነው ሲል፣ ክርስቶስ የአብን የልጅነት መብት የተቀበለ ነው ማለቱ ነው እንጂ፣ ክርስቶስ ከሌሎቹ ቀድሞ ተፈጥሯል ማለቱ አይደለም:: ክርስቶስ የፍጥረት አካል ነው ማለቱ ሳይሆን፣ ክርስቶስ ጌታዋ ነው ማለቱ ነው:: በዚህ መንገድ ራሱን በመግለጽ፣ የሐሰት መምህራኑ ሐሰተኛ አማልክት ለማንም ሰው የትኛውንም በረከት የመስጠት ኃይልም ሆነ ሥልጣን የላቸውም በማለት ጳውሎስ ግልፅ አድርጎ ያስቀምጣል:: የእግዚአብሔርን በረከቶች ሁሉ ሊወርስ የተገባውና ያንንም ለሌሎች ሊሰጥ የሚችል፣ በኵር ክርስቶስና ክርስቶስ ብቻ ነው::

ሦስተኛ፣ ጳውሎስ የሚለው ክርስቶስ የፍጥረት ወኪል ነው፣ እግዚአብሔር ፍጥረተ-ዓለሙን የፈጠረው በእርሱ ነው:: መጽሐፍ ቅዱስ ለእግዚአብሔርና ለክርስቶስ እንጂ ለመላእክት ያልሰጣቸውን የፍጥረት ዋና ዋና ሃላፊነቶች የአይሁድ ምሥጢራዊ ሃይማኖት ለመላእክት ይሰጣል:: በግሪክ ፍልስፍና ደግሞ፣ ቁስ አካላትና ሌሎች ስነ-ፈለካዊ ኃይላት

© 2010 by Third Millennium Ministries
www.thirdmill.org

ተመሳሳይ የሆኑ ሃላፊነቶች ይሰጣቸዋል፡፡ ጳውሎስ ግን የፍጥረት ጉዳይ የሚመለከተው ክርስቶስ ብቻ ነው፣ ስለዚህም ሌሎቹ ኃይላት ከእርሱ እጅግ የበታች ሲሆኑ ለእርሱም ይገዙለታል፡፡ በቆላስይስ ምዕራፍ 1 ቁጥር 16 የጻፈውን አድምጡ፡

> *እርሱም የማይታይ አምላክ ምሳሌ ነው፤ የሚታዩትና የማይታዩትም፥ ዙፋናት ቢሆኑ ወይም ጌትነት ወይም አለቅነት ወይም ሥልጣናት፥ በሰማይና በምድር ያሉት ሁሉ በእርሱ ተፈጥረዋልና ከፍጥረት ሁሉ በፊት በኵር ነው፤ ሁሉ በእርሱና ለእርሱ ተፈጥሮአል፤ (ቆላስይስ 1፡16)*

ቀደም ብለን እንደተመለከትነው፣ "አለቆችና ሥልጣናት" የሚሉት ቃላት የሚያመለክቱት፣ ኃይላትን ማለትም፣ በሐሰት መምህራኑ የሚመለኩትን ዲያቢሎሶች የመሳሰሉትን ነው፡፡ እንደ ጳውሎስ አገላለጽ ግን፣ እነዚህ አለቆችና ሥልጣናት ለክርስቶስ ይገዛሉ፡፡ የፍጥረት ሁሉ ጉዳይ ቀዳሚው ክርስቶስ ነው የሚለው መግለጫ እርሱ በፍጥረት ውስጥ ከሚገኙት ሁሉ እጅግ ይልቃል ማለት ነው፡፡

አራተኛ፣ ክርስቶስ የሁሉ የበላይ ጌታ ነው ምክንያቱም እግዚአብሔር የፍጥረት ሁሉ በኩር እንዲሆንና የቤተክርስቲያን ራስ እንዲሆን አድርጓልና ነው፡፡ በቆላስይስ ምዕራፍ 1 ቁጥር 18 ጳውሎስ የተናገረውን አድምጡ፡

> *እርሱም የአካሉ ማለት የቤተ ክርስቲያን ራስ ነው፤ እርሱም በሁሉ ፊተኛ ይሆን ዘንድ፥ መጀመሪያ ከሙታንም በኵር ነው። (ቆላስይስ 1፡18)*

ክርስቶስ በቤተክርስቲያን ከፍተኛ ሥልጣን እንደተሰጠውና ከሙታንም በኩር እንደሆነ ይህም "እርሱም በሁሉ ፊተኛ ይሆን ዘንድ" ነው በማለት ጳውሎስ መከራከሪያውን ያቀርባል፡፡

ይህም ማለት፣ እግዚአብሔር ፍጥረትን ያቀናበረው ክርስቶስ ኢየሱስን ከሁሉ የበላይ ለማድረግ ያለውን ዓላማ ከማስፈፀም አንፃር ነው ማት ነው፡፡ እግዚአብሔር አብ ወልድን ያከብረው ዘንድ፣ በሁሉም ላይ ገዢ ያደርገው ዘንድ ወደደ፡፡ እንግዲያው፣ የኢየሱስን ሉዓላዊነት ልቆ ለመገኘት ወይም ለመተካት የሚሞክር የትኛውም ሥርዓት ሐሰት ነው፡፡ ይህም ነገር፣ የግሪክን ፍልስፍናም ሆነ የአይሁድን ምሥጢራዊ ሃይማኖት ያካትታል፡፡

አምስተኛ፣ ክርስቶስ ሰው የሆነው አምላክ ነው በማለት ጳውሎስ ያብራራል፡፡ ይህ ድንቅ መግለጫ ገዢዎችና ሥልጣናት ተብለው ከተጠቀሱት ከግሪክ አምልኮተ ጣዖትና ከአይሁድ ምሥጢራዊ ሃይማኖት ሁሉ እጅግ የሚልቅ መሆኑን ያሳያል፡፡ ጳውሎስ በቆላስይስ 1፡19 የተናገራቸውን ቃላት እናድምጥ፡-

> *እግዚአብሔር ሙላቱ ሁሉ በእርሱ እንዲኖር፥ … ፈቅዶአልና። (ቆላስይስ 1፡19)*

ክርስቶስ ሉዓላዊው ትስጉተ እግዚአብሔር ይሆን ዘንድ፣ የእግዚአብሔር ሙላት በክርስቶስ እንዲኖር ፈቀደ፡፡ በቆላስይስ ሰዎች ይመለኩ የነበሩት ገዢዎችና ሥልጣናት እጅግ አናሳ መንፈሳዊ ፍጡራን ናቸው፡፡ ምንም እንኳን በግሪክ ፈላስፎች አንዳንድ ጊዜ አማልክት ተብለው ቢጠሩም፣ በጥቅሉ ግን የሉዓላዊነት መንበር በፍፁም ሊሰጣቸው አይችልም፡፡

በተቃራኒው ግን የእግዚአብሔር ሙላት በክርስቶስ ይኖራል፡፡ ይህም ማለት፣ ፍጥረታት ሁሉ ለጌታ ይታዘዙ ዘንድ፣ ክርስቶስ የፍጥረተ ዓለም ሁሉ ፈጣሪ ትስጉተ እግዚአብሔር ነው ማለት ነው፡፡ ይህም ክርስቶስ በሐሰት መምህራን ከሚመለኩት አናሳ መንፈሳዊ ፍጡራን እጅግ ይልቃል ማለት ነው፡፡

© 2010 by Third Millennium Ministries
www.thirdmill.org

በመጨረሻ፣ አዳምንና እግዚብሔርን ያስታረቀ ብቸኛ አስታራቂ ክርስቶስ እንደሆነ ጳውሎስ ያብራራል፡፡ ጳውሎስ ስለ ክርስቶስ የተነገረውን ይህን ጭብጥ በቆላስይስ ምዕራፍ 1 ቁጥር 19 እና 20 ውስጥ ያብራራል፡-

> ***እግዚአብሔር ሙላቱ ሁሉ በእርሱ እንዲኖር፥ በእርሱም በኩል በመስቀሉ ደም ሰላም አድርጎ በምድር ወይም በሰማያት ያሉትን ሁሉ ለራሱ እንዲያስታርቅ ፈቅዶአልና። (ቆላስይስ 1፡19-20)***

እግዚአብሔር "በኢየሱስ አማካይነት ሁሉን ያስታርቅ ዘንድ አቀደ"፡፡ ያም ማለት፣ እግዚአብሔር ኃጢአትን ከምድረ ገፅ በማጥፋት ከሰው ዘር ጋር ሰላምን የፈጠረበት መንገድና ወኪል ኢየሱስ ክርስቶስ ነው ማለት ነው፡፡

በሐሰት መምህራን የሚመለኩት ደካማ ኃይላት አጋንንቶች ናቸው፣ የሚያመልኳቸውን ይጨቁኑና ያስፈራሩ ዘንድ የክርስቶስን ክብርና ሥልጣን በስርቆቻ የራሳቸው ለማስመሰል ይጥራሉ፡፡ ግባቸው እርባና ቢስ ሲሆን፣ የሚያመልኳቸውን ትርጉም በሚሰጥ መንገድ የመባረክ አቅም የላቸውም፡፡ ክርስቶስ ግን ወደ እግዚአብሔር የሚያደርስ መንገድ ነው፡፡ ጳውሎስ የሚሰብከው ወንጌል እግዚአብሔር ፍጥረተ ዓለሙን ኃጢአት ወደማይኖርበት፣ ልዕልና ወደሚገኝበት እና ዘላለማዊ በረከት ወደሞላበት ሁኔታ እንደሚያሸጋግር ይናገራል፡፡ ይህንንም የሚያደርገው በኢየሱስ ክርስቶስ፣ እና በኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ ነው፡፡ ኃጢአት ይቅር የሚባለውና የእግዚአብሔር በጎነት የሚገኘው በኢየሱስ ብቻ ነው፡፡ የሐሰት መምህራኑ በሚያራግቧቸው እርባና ቢስና ኃይል አልባ መናፍስት ጉዳይ መጨነቅ አይገባም፡፡ በኢየሱስ ወደ እግዚአብሔር የመግባትና ዘላለማዊ በረከቶቹን የመቀበል ነፃ ዕድል አግኝተናል፡፡

ቢያንስ በእነዚህ ስድስት መንገዶች፣ ክርስቶስ የእግዚአብሔር አምሳል፣ የፍጥረት በኵር፣ የፍጥረት ወኪል፣ ሉዓላዊ ጌታ፣ ትስጉተ እግዚአብሔር እና ብቸኛው አስታራቂ መሆኑን አረጋግጠናል፡፡ በቆላስይስ የሚገኙ የሐሰት መምህራን ከሚያመልኳቸው አማልክት ተብዬዎች ሁሉ ኢየሱስ እጅግ ይልቃል!

## የክርስቶስ አገልጋዮች የበላይነት

ጳውሎስ ክርስቶስ ከመንፈሳዊ ኃይላት ሁሉ የሚልቅ መሆኑን በማሳየት፣ የክርስቶስን አገልጋዮች የበላይነት አስረግጦ ይናገራል፡፡ ይህ የመከራከሪያ ሃሳቡ በቆላስይስ ምዕራፍ 1 ከቁጥር 21 እስከ ምዕራፍ 2 ቁጥር 5 ውስጥ ይገኛል፡፡

ክርስቶስ ከሐሰት አማልክት የበላይ በመሆኑ ምክንያት፣ የክርስቶስ አገልጋዮች ደግሞ የሐሰት አማልክትን ከሚያገለግሉት ሁሉ የበላይ ናቸው በማለት ጳውሎስ መከራከሪያውን ያቀርባል፡፡ የጳውሎስ መከራከሪያ አምስት ነጥቦችን ያዘለ ሃሳብ ነው፡- በቆላስይስ ምዕራፍ 1 ከቁጥር 21 እስከ 23 እና በምዕራፍ 2 ቁጥር 5 የጠቀሰው፣ በክርስቲያኖች ወንጌል አማካይነት የተገኘው እርቅ፤ በቆላስይስ ምዕራፍ 1 ቁጥር 24 የተጠቀሰው የጳውሎስ መከራና የሚያስገኘው ውጤት፤ በቆላስይስ ምዕራፍ 1 ቁጥር 25 የጠቀሰው የጳውሎስ መለኮታዊ ተልዕኮ፤ በቆላስይስ ምዕራፍ 1 ከቁጥር 25 እስከ 28 እና በምዕራፍ 2 ከቁጥር 2 እስከ 4 የተጠቀሰው በወንጌል አማካይነት የተገኘው ከሁሉ የሚልቅ መገለጥ፤ ጳውሎስ በቆላስይስ ምዕራፍ 1 ቁጥር 29 እስከ ምዕራፍ 2 ቁጥር 1 የጠቀሰው የክርስቶስን አገልጋዮች ለማስታጠቅ ስለሚያደረገው ተጋድሎ ናቸው፡፡

ጳውሎስ የሚጀምረው የቆላስይስ ሰዎች በወንጌል አማካይነት በተቀበሉትና እያጣጣሙት ባለው እርቅ ላይ በማትኮር ነው፡፡ በቆላስይስ 1 ከቁጥር 22 እስከ 23 እንዲህ እናነብባለን፡-

> ***እናንተንም ነውርና ነቀፋ የሌላችሁና ቅዱሳን አድርጎ በእርሱ ፊት ያቀርባችሁ ዘንድ፥ …***

© 2010 by Third Millennium Ministries
www.thirdmill.org

*በሥጋው ሰውነት በሞቱ በኩል አስታረቃችሁ።*
*ይህም፥ ተመሥርታችሁና ተደላድላችሁ ከሰማችሁትም ከወንጌል ተስፋ ሳትናወጡ፥*
*በሃይማኖት ጸንታችሁ ብትኖሩ ይሆናል፤ ያም ወንጌል ከሰማይ በታች ባለው ፍጥረት ሁሉ*
*ዘንድ የተሰበከ ነው፥ እኔም ጳውሎስ የእርሱ አገልጋይ ሆንሁ። (ቆላስይስ 1፡22-23)*

የክርስቶስ አገልጋዮች የበላዮች ናቸው ምክንያቱም የሚሰብኩት ወንጌል የሚያምኑትን ከእግዚአብሔር ጋር የሚያስታርቅ ነውና፡፡

በቆላስይስ የሚገኙ የሐሰት መምህራን አጋንንቶችን መለማመንን እያበረታቱ፣ ከእግዚአብሔር ጋር እርቅን እናመጣለን ብለው ይናገራሉ፡፡ ወደ እውነቱ ስንመጣ ግን፣ ወንጌላችን ብለው የሚጠሩት ስብከታቸው የማዳን ኃይል ስለሌለው እርቅ ሊያስገኝላቸው ጨርሶውኑ አልቻለም፡፡

በተቃራኒው ግን፣ የቆላስይስ አማኞች በእግዚአብሔር አገልጋዮች በተሰበከላቸው እውነተኛ ወንጌል አማካይነት እውነተኛውን እርቅ እያጣጣሙ ናቸው፡፡ እነርሱ አሁን ይቅር ተብለውና የክርስቶስን ጽድቅ ለብሰው በእግዚአብሔር ፊት ቆመዋል፡፡ ይህም ጳውሎስ የሚነግራቸውን እንዲያምኑና የሐሰት መምህራኑን እንዲቃወሙ ሊያበረታታቸው ይገባል፡፡

ሁለተኛ፣ ጳውሎስ ስለ መከራው ይናገራል፣ ንግግሩም ስለ ቤተክርስቲያን በሚቀበለው መከራ ላይ ያተኩራል፡፡ በቆላስይስ ምዕራፍ 1 ቁጥር 24 እንዲህ ሲል ጽፏል፡-

*አሁን በመከራዬ ስለ እናንተ ደስ ይለኛል፥ ስለ አካሉም ማለት ስለ ቤተ ክርስቲያን በሥጋዬ በክርስቶስ መከራ የጐደለውን እፈጽማለሁ። (ቆላስይስ 1፡24)*

ቀደም ባለው ትምህርት እንደተመለከትነው፣ የጳውሎስ መከራ ለወንጌል ብርቱ ምስክር በመሆን፣ ቤተክርስቲያንን በማበረታታት፣ በክርስቶስም መከራ የጎደለውን በመፈጸም ለቤተክርስቲያን በረከት ሆኗል፡፡ በተቃራኒው ግን በቆላስይስ ይኖሩ የነበሩ የሐሰት መምህራን ታስረውም መከራ ደርሶባቸውም አያውቅም፡፡ ጳውሎስ ስለ ቤተክርስቲያን መከራን ለመቀበል ያለውን ፈቃደኝነት አጽንዖት በመስጠት፣ የክርስቶስ አገልጋዮች ከሐሰት መምህራኑ ይልቅ ስለ ህዝባቸው ግድ የሚላቸው መሆኑን በግልጽ አስቀምጧል፡፡

ሦስተኛ፣ ጳውሎስ ስተቀበለው መለኮታዊ ተልዕኮ ተናግሯል፡፡ በቆላስይስ ከሚገኙትና ራሳቸውን ከሾሙት የሐሰት መምህራን በተቃራኒው፣ ጳውሎስ የሐዋርያነት ሥልጣን የተሰጠው በጌታ በራሱ ነው፡፡ ጳውሎስ ይህንን ተልዕኮውን በቆላስይስ ምዕራፍ 1 ቁጥር 25 ውስጥ እንዲህ ገልፆታል፡-

*ስለ እናንተ እንደ ተሰጠኝ እንደ እግዚአብሔር መጋቢነት፥ የእግዚአብሔርን ቃል ፈጽሜ እንድሰብክ እኔ የቤተ ክርስቲያን አገልጋይ ሆንሁ፤ (ቆላስይስ 1፡25)*

በዚህ ስፍራ እንደምናየው፣ ጳውሎስን የጠራው እግዚአብሔር ነው፡፡

ጳውሎስ በወጣትነቱ ዘመን፣ በታላቅ ቅናት ቤተክርስቲያንን ያሳድድ ነበር፡፡ በኋላ ግን፣ ከሞት የተነሣው ጌታ ኢየሱስ ለጳውሎስ ተገለጠለትና ለወጠው፡፡ በዚህ ወቅት፣ ጳውሎስ የእርሱ ሐዋርያ እንዲሆን ኢየሱስ ሾመው፣ በኢየሱስም ስም እንዲናገርም ሥልጣንን ሰጠው፡፡ ይህም ማለት የጳውሎስ ሥልጣን ከሐሰት መምህራኑ እጅግ የይበልጣል ማለት ነው፡፡

© 2010 by Third Millennium Ministries
www.thirdmill.org

ጳውሎስ በቆላስይስ ምዕራፍ 2 ቁጥር 8 ውስጥ አስተምህሯቸውን እንዲህ ይገልጸዋል፡-

> ***እንደ ክርስቶስ ትምህርት ሳይሆን፥ እንደ ሰው ወግና እንደ ዓለማዊ እንደ መጀመሪያ ትምህርት ባለ በፍልስፍና በከንቱም መታለል ማንም እንዳይማርካችሁ ተጠበቁ። (ቆላስይስ 2፡8)***

የሐሰት መምህራኑ የሚደገፉት ጣዖት አምላኪ ሰብዓዊ ፍጡራን በፈለሰፏቸው ሃሳቦች ላይ ነው፡፡ እንደ ጳውሎስ፣ ስለ እግዚአብሔር የመናገር ሥልጣን አልተሰጣቸውም ደግሞም ቤተክርስቲያንን እንዲያስተምሩ እግዚአብሔር አልጠራቸውም፡፡

አራተኛ፣ የሐሰት መምህራኑ ከሚናገሩት ይልቅ ጳውሎስ የተቀበለው መገለጥ እጅግ ይልቃል፡፡ ለምሳሌ፣ ጳውሎስ በቆላስይስ ምዕራፍ 2 ቁጥር 4 የተናገረውን እናዳምጥ፡-

> ***ማንም በሚያባብል ቃል እንዳያስታችሁ ይህን እላለሁ። (ቆላስይስ 2፡4)***

ጳውሎስ የሐሰት መምህራኑን ንግግር "አሳሳች" ይለዋል፡፡ በተቃራኒው ግን፣ የእርሱ ንግግሮች እውነቱን ይገልጣሉ፣ ክርስቲያኖችም የሐሰት አስተማሪዎቹን ማሳሳት እንዲያቃልሉ ያግዛቸዋል፡፡

እንዲያውም፣ በገላትያ ምዕራፍ 1 ከቁጥር 15 እስከ 18 እንደምንመለከተው፣ ጳውሎስ ከእግዚአብሔር መገለጥን እየተቀበለ በደማስቆ በረሐ ሦስት ዓመታትን አሳልፏል፡፡ የሐሰት መምህራኑ ግን፣ ይታመኑ የነበሩት ከትውልድ ወደ ትውልድ ሲወርድ ሲዋረድ በኖረው ትውፊት ላይ ነበር፡፡ ይህም ጳውሎስ የጠቀበለውን መገለጥ ከሐሰት መምህራኑ እጅግ እንዲልቅ ያደርገዋል፡፡

እንግዲህ፣ ጳውሎስ ከእግዚአብሔር የተቀበለው መገለጥ፣ በቆላስይስ ይኖሩ እንደነበሩት የሐሰት መምህራን በከንቱ የሰብዓዊ ፍጡራን ልብ ወለድ ላይ የተመሠረተ አለመሆኑ እጅግ ወሳኝነት አለው፡፡ ከሁሉ እጅግ ወሳኝ የሆነው ደግሞ፣ የጳውሎስ መገለጥ የተሸከመው ይዘት በቆላስይስ ይኖሩ ከነበሩት የሐሰት መምህራን አስተምህሮ እጅግ የሚልቅ መሆኑ ነው፡፡ ጳውሎስ ለቆላስይስ ቤተክርስቲያን በጻፈው መልእክት እንደገለጠው፣ መገለጡን እግዚአብሔር ለእርሱ የገለጠለት "ምሥጢር" እና "የጥበብና የእውቀት ሁሉ ባለጠግነት" በማለት ይገልጸዋል፡፡ ታዲያ ጳውሎስ ይህንን ሐብት ለራሱ ብቻ አላስቀረውም፣ በስብከተ ወንጌሉ ለህዝብ ሁሉ ያዳረሰው ነበር፡፡ ይህ ሀብት ከእግዚአብሔር የመታረቅን እውነታ፣ በመንግሥቱ ውስጥ ባለድርሻ መሆንን፣ በክርስቶስ መስዋዕትነት ምክንያትና በእምነት መቀበልን ያካተተ ነው፡፡ ይህ አዋጅ የሐሰት መምህራኑ ከሚያቀርቡት ከየትኛውም ማባበያ እጅግ ይልቃል፡፡

ጳውሎስ የሚያነሳው አምስተኛ ሃሳብ፣ የክርስቶስ አገልጋዮች ስለተቀበሉት ኃይል የበላይነት ሲሆን፣ ይህንንም እግዚአብሔር ለአገልጋዮቹ ኃይልን ሰጥቷል በማለት ይገልጠዋል፡፡ ጳውሎስ የሚደክመው በራሱ ኃይል አልነበረም፡፡ ይልቁኑ፣ ጳውሎስ እንደ እርሱ ሐዋርያ እንዲሠራና መከራን እንዲቀበል እግዚአብሔር ኃይል ይሰጠውና ያበረታታው ነበር፡፡ መንፈስ ቅዱስ ጳውሎስን በአስገራሚ ስጦታዎች የሞላው ሲሆን፣ የሚናገራቸውን ቃላት እና የሚናገርበትንም ዕድሎች ይፈጥርለት፣ ምስክርነቶቹን የሚያጸኑ ተዓምራትን እንዲያደርግና የእግዚአብሔርን መንግሥት በምድር እንዲያሰፋ ጳውሎስን ያስችለው ነበር፡፡ ጳውሎስ በቆላስይስ ምዕራፍ 1 ቁጥር 29 እንዲህ አስቀምጦታል፡-

> ***ለዚህም ነገር ደግሞ፥ በእኔ በኃይል እንደሚሠራ እንደ አሠራሩ እየተጋደልሁ፥ እደክማለሁ። (ቆላስይስ 1፡29)***

© 2010 by Third Millennium Ministries
www.thirdmill.org

የጳውሎስ ሥልጣን፣ ቃሎችና ኃይል ከእግዚአብሔር የሚመጣ ነበር፡፡ ስለዚህ በቆላስይስ ይኖሩ ከነበሩት የሐሰት መምህራን ጋር ሊነፃፀር አይችልም፡፡ የእርሱ አገልግሎትና መልእክት ኃይል አልባና ትርጉም የለሽ ነበር፡፡

ስናጠቃልለው፣ ጳውሎስ በክርስቲያኖች ወንጌል አማካይነት ስለተገኘው እርቅ፣ ለቤተክርስቲያን ሲል ስለተቀበለው መከራ፣ ስለ መለኮታዊ ተልዕኮው፣ ስለ ተቀበለው መገለጥ እና ከመንፈስ ቅዱስ ስለተቀበለው ኃይል አጽንዖት በመስጠት የክርስቶስን አገልጋዮች የበላይነት አስረግጦ እንደተናገረ አይተናል፡፡

## በክርስቶስ የተገኘው ድነት የበላይነት

ጳውሎስ የክርስንና የአገልጋዮቹን የበላይነት በአጽንዖት ከጠቀሰ በኋላ በሦስተኛ ደረጃ የሚያነሳው፣ በምዕራፍ 2 ከቁጥር 6 እስከ 23 የተጠቀሰውን በክርስቶስ የተገኘውን ድነት የበላይነት ነው፡፡

ጳውሎስ በክርስቶስ ስለተገኘው ድነት የሚያቀርበው ሃሳብ በሁለት ዐቢይ ክፍሎች ይከፈላል፡ በቆላስይስ ምዕራፍ 2 ከቁጥር 6 እስከ 15 ባለው ውስጥ የተጠቀሰውና ከክርስቶስ ጋር ባለ አንድነት ስለሚገኘው ሕይወት ያቀረበው ምሥጋና፣ በቆላስይስ ምዕራፍ 2 ከቁጥር 16 እስከ 23 በሚገኘው ክፍል የተጠቀሰው ለተለያዩ ወጎችና ልማዶች የመገዛትን ሕይወት ያወገዘበት ናቸው፡፡

በመጀመሪያው ክፍል፣ በክርስቶስ በመሆን በተገኘው ድነት የሚገኙ በርካታ ጥቅሞችን ጳውሎስ ያመለክታል፣ የሚያስቀድመውም በምዕራፍ 2 ከቁጥር 6 እስከ 10 በተጠቀሰው በጎነትን በተሞላውና እኛንም በሚያበረታታን በክርስቶስ ጌትነት ነው፡፡

በእነዚህ ጥቅሶች ውስጥ፣ ክርስቶስ ጌታችን ስለሆነ፣ እኛም በእርሱ ተተክለናል፣ ተገንብተናል፣ እጅግም በርትተናል ከዚያ የተነሳም እኛ በታላቅ ምሥጋና ተሞልተናል በማለት ጳውሎስ ይጠቅሳል፡፡ የሐሰት መምህራንን የሚከተሉት ግን ለማይረቡ መንፈሳዊ ኃይላት ተገዢ ናቸው፣ በክርስቶስ ጌትነት ስር ያሉት ግን ከእርሱ ጋር የመግዛት ሥልጣን ተሰጥቷቸዋል፡፡ ጳውሎስ በቆላስይስ ምዕራፍ 2 ቁጥር 9 እስከ 10 እንዲህ ጽፏል፡-

> ***በእርሱ የመለኮት ሙላት ሁሉ በሰውነት ተገልጦ ይኖራልና፤***
> ***ለአለቅነትና ለሥልጣንም ሁሉ ራስ በሆነ በእርሱ ሆናችሁ ተሞልታችኋል።***
> ***(ቆላስይስ 2፡9-10)***

ክርስቶስ ከየትኞቹም ኃይላት እጅግ የሚልቅ መለኮታዊ ሥልጣን አለው፡፡ አማኞችም ከእርሱ ጋር በመተባበራቸው የዚያ መለኮታዊ ሥልጣን ተካፋዮች ናቸው፡፡

ሁለተኛ፣ አማኞች ከክርስቶስ ጋር ከመተባበራቸው የተነሳ ስለተቀበሉት መንፈሳዊ ወሳኝ በረከት ጳውሎስ ይገልጣል፡፡ ጳውሎስ ይህንን በረከት በቆላስይስ ምዕራፍ 2 ከቁር 11 እስከ 13 አብራርቶታል፡፡ ለምሳሌ፣ በቆላስይስ ምዕራፍ 2 ቁጥር 12 እንዲህ ጽፏል፡

> ***በጥምቀትም ከእርሱ ጋር ተቀብራችሁ፥ በጥምቀት ደግሞ፥ ከሙታን ባስነሣው በእግዚአብሔር አሠራር በማመናችሁ፥ ከእርሱ ጋር ተነሣችሁ። (ቆላስይስ 2፡12)***

ከክርስቶስ ጋር በመተባበራችን ምክንያት፣ አማኞች ተካፋይ የሚሆኑትይቅርታን ካገኘንበት፣ ከክርስቶስ ሞት ጋር ብቻ ሳይሆን፣ የመንፈሳችንን ዳግም ልደት ካገኘንበት ከክርስቶስ ትንሣኤና ሕይወትም ጋር እንካፈላለን፡፡

© 2010 by Third Millennium Ministries
www.thirdmill.org

ሦስተኛ፣ አማኞች ከክርስቶስ ጋር በመተባበራቸው ምክንያት፣ የኃጢአትን ይቅርታ ተቀብለናል፣ የህግንም ትዕዛዛት በመፈፀም በሥራ መዳንን ለመቀበል ከመፍጨርጨር ነጻ ወጥተናል፡፡ ጳውሎስ እነዚህን ሃሳቦች በቆላስይስ ምዕራፍ 2 ከቁጥር 13 እስከ 15 ጠቅሷቸዋል፡፡ በቁጥር 14 እና 15 እንዲህ ጽፏል፡-

***በእኛ ላይ የነበረውን የሚቃወመንንም በትእዛዛት የተጻፈውን የዕዳ ጽሕፈት ደመሰሰው፤ እርሱንም በመስቀል ጠርቆ ከመንገድ አስወግዶታል፤ አለቅነትንና ሥልጣናትን ገፎ፥ ድል በመንሣት በእርሱ እያዞራቸው በግልጥ አሳያቸው። (ቆላስይስ 2፡14-15)***

የእግዚአብሔር ህግ የወደቀውን የሰው ዘር ይኮንናል፡፡ እኛ ግን ከክርስቶስ ሞት ጋር በመተባበራችን፣ ህጉ የሚጠይቀውን ሞት ሞተናል፡፡ በህጉ የተጻፈብን ትዕዛዝም ተደምስሷል፣ ስለዚህ አሁን እኛ ኩነኔ የለብንም፡፡

በክርስቶስ አማካይነት ከተቀበልናቸው ከእነዚህ በረከቶች ጀርባ፣ የሐሰት መምህራን የሚያናፍሱትን መልእክት ጳውሎስ ይረግመዋል፡፡ ከክርስቶስ ጋር የመተባበር ሕይወት ከክርስቶስ በተገኙት በረከቶች ተለይቶ ይታወቃል፡፡ ለወግና ለሥርዓት ተገዢ የሆነ ሕይወት ግን በሰዎች አምባገነናዊ ጌትነት ስር ይወድቃል፡፡ ጳውሎስ በቆላስይስ ምዕራፍ 2 ከቁጥር 16 እስ 18 እንደጻፈው፣ ይህም ሁኔታ በሰው ፍርድ ስር መጣሉ ብቻ ሳይሆን፣ በክርስቶስ ከሚገኙ በረከቶችም ውጪ ያደርጋል፡፡

በተጨማሪም፣ ከክርስቶስ ጋር መተባበር ወሳኝ መንፈሳዊ ሕይወት ሲያስገኝ፣ ለዚህ ዓለም ሥርዓት መገዛት ደግሞ ከክርስቶስ መለየትን ያስከትላል፡፡ ጳውሎስ በቆላስይስ ምዕራፍ 2 ቁጥር 19 እንዳመለከተው፣ ይህ ሁኔታ በመንፈስ ከመበርታት ይልቅ ደካማ ያደርጋል፣ መንፈሳዊ እድገትንም ያቀጭጫል፡፡

በመጨረሻም፣ ከክርስቶስ ጋር መተባበር ይቅርታን ሲያስገኝና አማኙን ከህግ እርግማን ነፃ ሲያወጣ፣ ለዚህ ዓለም ሥርዓት መገዛት ግን ለምናኔ ይዳርጋል፡፡ ጳውሎስ ይህንን መሳዩን የምናኔ እርባና ቢስነት በቆላስይስ ምዕራፍ 2 ቁጥር 23 እንዲህ በመጻፍ አጣጥሎታል፡

***ይህ እንደ ገዛ ፈቃድህ በማምለክና በትሕትና ሥጋንም በመጨቆን ጥበብ ያለው ይመስላል፥ ነገር ግን ሥጋ ያለ ልክ እንዳይጠግብ ለመከልከል ምንም አይጠቅምም። (ቆላስይስ 2፡23)***

በቆላስይስ ለሚገኙ የሐሰት መምህራን አማልክት መገዛት ለኃጢአት ምንም ፋይዳ ለሌለው ጨቋኝ የሕይወት ዘይቤ ታልፎ መሰጠት ነው፡፡ ምንም እንኳን ይህ የጉስቁልና ኑሮ ወደ በረከት ያደርሳል ተብሎ ቢገመትም፣ አጋንንቶች ግን ማንንም የመባረክ ኃይል የላቸውም፡፡ በተቃራኒው ግን፣ ከክርስቶስ ጋር መተባበር ከባርነት ይልቅ ነጻነትን የሚያስገኝ ሲሆን፣ በአማኙ ላይ የተጫነውን የኃጢአት ኃይል ይሰባብራል፡፡

ከክርስቶስ ጋር በመተባበር የሚገኘውን ሕይወትና ለሰው ወግና ሥርዓት ተገዢ የመሆንን ሕይወት በማነጻጸር፣ በእውነተኛው የክርስቲያን ወንጌል ስብከት የሚገኘው ድነት በቆላስይስ ይኖሩ የነበሩ የሐሰት መምህራን በማስመሰል ከሚያቀርቧቸው በረከት ተብዬዎች እጅግ እንደሚልቅ ጳውሎስ አመልክቷል፡፡

© 2010 by Third Millennium Ministries
www.thirdmill.org

## የክርስቲያናዊ አኗኗር የበላይነት

በስተመጨረሻም፣ ጳውሎስ የክርስቶስንና የአገልጋዮቹን የበላይነት ደግሞም በክርስቶስ ወንጌል የተገኘውን ድነት ከዳሰሰ በኋላ፣ በቆላስይስ ምዕራፍ 3 ከቁጥር 1 እስከ ምዕራፍ 4 ቁጥር 6 ድረስ ወደ ጠቀሰው የክርስቲያናዊ አኗኗር የበላይነት ይሸጋገራል፡፡ ጳውሎስ በዚህ ክፍል የገለጠው፣ ክርስቲያናዊው የአኗኗር ዘይቤ በሐሰት መምህራኑ ጥብቅና ከሚቆምለት ሕይወት ይልቅ እጅግ ሥርዓት ያለው መሆኑን ነው፡፡

በቆላስይስ ይኖሩ የነበሩ የሐሰት መምህራን ስለ ግበረገብ እጅግ ግድ የሚላቸው ይመስላሉ፡፡ እነዚያን ሁሉ ጨቋኝ የአኗኗር ዘይቤዎች በሰው ላይ የሚጭኑት የሥጋን ልቅነት ለመግራት ነው፡፡ በአንዳንድ ሁኔታዎችም፣ ይህ የእነርሱ ግብረገባዊ ልክ ወይም ግብ እነዚን መሳይ ኃጢአጦች አስመልክቶ የክርስቲያኖቹ ቤተክርስቲያን ከሚያስተምሩት ጋር ስምምነት ያለው ይመስላል፡፡ ችግሩ ያለው አቀራረባቸው ላይ ነው፡፡ በአጭሩ፣ አትቅመስ አትንካ የሚለው ወግ አያዋጣም! የጉዳዩ ጭብጥ ያለው የወደቀው የሰው ዘር ኃጢአትን መቋቋም የሚችልበት አቅም የሌለው መሆኑ ነው፡፡ ስለዚህ፣ ኃጢአትን ለማስወገድ የቱንም ያህል ብንጥር፣ ዘወትር ወድቀን እንገኛለን፡፡ ይህም ማለት፣ ግብረገባዊ ሕይወት ለመምራት፣ እግዚአብሔር ያስቀመጠልንን ግብረገባዊ ልክ ለመፈፀም የምንሻ ከሆነ፣ ከእኛ እጅግ ብርቱ በሆነና በሚበልጥ ስብዕና መታመን ይገባናል፡፡

በአንዳንድ መንገዶች፣ ጳውሎስ ስለ ክርስቲያናዊ አኗኗር የሰጣቸው ትምህርቶች ከሐሰት መምህራኑ ጋር ይስማማል፡፡ እንዲውም፣ ጳውሎስ እጅግ ነገሩን ወደ ላቀ ደረጃ በመውሰድ ምድራዊ ነገርን ከማሳደድ ይልቅ፣ ሰማያዊና መንፈሳዊ በሆነ ነገር ላይ ማተኮር እጅግ አስፈላጊ መሆኑን ይጠቅሳል፡፡ በቆላስይስ ምዕራፍ 2 ቁር 2 የጠቀሰውን እናድምጥ፡-

> *በላይ ያለውን አስቡ እንጂ በምድር ያለውን አይደለም። (ቆላስይስ 3፡2)*

እንደ ጳውሎስ አገላለጥ፣ ከምድራዊ ነገር ይልቅ ለመንፈሳዊና ለሰማያዊ ነገሮች የበለጠ ዋጋ እንድንሰጥ ያሳስበናል፡፡ ይህ አመለካከት በብህትውና አስተማሪዎቹም ቢያንስ ለይስሙላ ያህል ይነሳል፡፡ ልክ እንደ ብህትውና አስተማሪዎቹ ሁሉ፣ ጳውሎስም የሥጋን ፈተና ስለመቋቋም በብርቱ ያስተምራል፡፡ ለምሳሌ፣ በቆላስይስ ምዕራፍ 3 ቁጥር 5 ጳውሎስ እንዲህ ጽፏል፡

> *እንግዲህ በምድር ያሉቱን ብልቶቻችሁን ግደሉ፥ እነዚህም ዝሙትና ርኵሰት ፍትወትም ክፉ ምኞትም ጣኦትንም ማምለክ የሆነ መጎምጀት ነው፤ (ቆላስይስ 3፡5)*

የሥጋ ፈተና ክፉ ስለ መሆኑ ጳውሎስ ከሐሰት መምህራኑ ጋር ይስማማል፡፡ እርሱ የማይስማማው ኃጢአትን እንዴት እናስወግድ በሚለው ነው፡፡

ጳውሎስና የሀሰት ምህራኑ የሚለያዩባቸው ሌሎችም በርካታ መንገዶች አሉ፡፡ ለምሳሌ፣ ምንም እንኳን የሐሰት መምህራኑ ለማስመሰል ያህል በሰማያዊ ነገሮች ላይ ማትኮር እንዳለብን እናምናለን ቢሉም ጳውሎስ የነቀፈው አስተምህሯቸው ግን ምድራዊ ነበር፡፡ ምንም እንኳን መንፈሳዊ የመሆን ግብ ያላቸው ቢመስሉም፣ ወደዚያ ግብ ለመድረስ የሚጥሩት ግን በምድራዊ ጉዳዮች ላይ በማትኮር ነው፡፡ በቆላስይስ ምዕራፍ 2 ቁር 22፣ ጳውሎስ አስተምህሯቸውን እንዲህ ጠቅለል አድርጎ ያቀርበዋል፡-

> *አትያዝ፥ አትቅመስ፥ አትንካ (ቆላስይስ 2፡22)*

© 2010 by Third Millennium Ministries
www.thirdmill.org

ባህታውያኑ ሰውን ወደ መንፈሳዊው ዓለም እንመራለን ቢሉም፣ አስተምህሯቸው ግን ተራና፣ ምድራዊ በሆኑ ጉዳዮች ላይ ያተኮረ ነበር፡፡

ባህታውያኑ በብህትውና ልምምዶቻቸው እጅግ የተወጠሩ ቢመስሉም እውነተኛ ሰማያዊና መንፈሳዊ ስሆኑ ትክክለኛ ነገሮ ግን እብዛም ግድ አልነበራቸውም፡፡ ግባቸው መንፈሳዊ ይምሰል እንጂ፣ ጥረታቸው ሁሉ ግን በምድራዊ ነገሮች ላይ ያጠነጠነ ነበር፡፡

በሌላው ወገን፣ ጳውሎስ፣ አማኞች መንፈሳዊ በሆኑ ጉዳዮች ላይ ሊያተኩሩ የሚችሉባቸውን ግልፅና ውሱን ጉዳዮች ያስተምር ነበር፡፡ ኃጢአት መሥራታቸውን እንዲያቆሙ በብርቱ ቢያሳስብም፣ ይህን ማድረግ ግን ለወደቀው ሰብዓዊ አስተሳሰብ የሚቀና እንደማይሆን ያውቅም ነበር፡፡ በቆላስይስ ምዕራፍ 3 ከቁጥር 9 እስከ 11 የተናገረውን እናድምጥ፡-

> ***እርስ በርሳችሁ ውሸት አትነጋገሩ፥ አሮጌውን ሰው ከሥራው ጋር ገፈፋችሁታልና፥ የፈጠረውንም ምሳሌ እንዲመስል እውቀትን ለማግኘት የሚታደሰውን አዲሱን ሰው ለብሳችሁታል፤***
> ***በዚያም የግሪክ ሰው አይሁዳዊም የተገረዘም ያልተገረዘም አረማዊም እስኩቴስም ባሪያም ጨዋ ሰውም መሆን አልተቻለም፥ ነገር ግን ክርስቶስ ሁሉ ነው፥ በሁሉም ነው።***
> ***(ቆላስይስ 3፡9-11)***

በስነ-ምግባር ለታነፀ አኗኗር ቁልፉ፤ አማኞች ከክርስቶስ ጋር መተባበራቸው ነው፣ ክርስቶስ ሁሉ ነው በሁሉም ነወ በማለት ጳውሎስ ያብራራል፡፡ ከክርስቶስ ጋር ካለን ከዚህ መተባበር የተነሳ፣ እኛ "አዲስ ማንነት" ወይም "አዲስ ፍጥረትነት" አግኝተናል፡፡ እናም በእግዚአብሔር ውስጣዊ መታደስን እናገኛለን፡፡ ይህ ትብብርና ተሃድሶ በስነ-ምግባር ታንፀን እንድንኖር ያስችለናል፡፡

የሐሰት መምህራን እውነተኛ አማኞች አይደሉም፡፡ በወንጌል አያምኑም፣ ስለዚህም ከክርስቶስ ጋር ኅብረት የላቸውም፡፡ አዲሰ ተፈጥሮ የላቸውም፣ ስለዚህም በእግዚአብሔር ተሃድሶን አያገኙም፡፡ በውጤቱም፣ ከኃጢአት ለመራቅ የሚያደርጉት ሙከራ ለውድቀት የተዳረገ ነው፡፡

ሆኖም ግን፣ አማኞች፣ ከክርስቶስ ጋር ኅብረት አላቸው፣ እናም የእግዚአብሔርን የስነ-ምግባር ደረጃዎች ማሟላት የሚችበትን ኃይል ያገኛሉ፡፡ ጳውሎስ ግን በዚህ ሃሳብ አያቆምም፡፡ ይልቁኑ፣ ክርስቲያኖች ኃጢአትን በራሳቸው ኃይል ለመግታት ከመጣጣር ይልቅ በእግዚአብሔር ኃይል በመታመን ሊሄዱባቸው የሚገባቸውን ተግባራዊ መንገዶች ያመለክታል፡፡ በቆላስይስ ምዕራፍ 3 ቁጥር 12 የሰጠውን መመሪያ እናድምጥ፡,

> ***እንግዲህ እንደ እግዚአብሔር ምርጦች ቅዱሳን ሆናችሁ የተወደዳችሁም ሆናችሁ፥ ምሕረትን፥ ርኅራኄን፥ ቸርነትን፥ ትህትናን፥ የዋህነትን፥ ትዕግሥትን ልበሱ፤ (ቆላስይስ 3፡12)***

አማኞች በስነ-ምግባር የታነፀ ሕይወት ለመኖር ከፈለጉ ርኅራኄ እና ቸርነትን በመሳሰሉ ሰማያዊ ነገሮች ላይ ማትኮር እንጂ ሊያስወግዱት በሚፈልጉት ኃጢአት ላይ ማትኮር እንደሌለባቸው ጳውሎስ ይመክራል፡፡ በስነ-ምግባር የታነፀ ሕ\ወት እንድንኖር ሊያበረታታን የሚገባው እግዚአብሔር ለእኛ ያለው ፍቅር እና ምርጫ እንጂ የሐሰት አማልክትን በመለማመን ላይ በሚያተኩረው ጥረታችን ላይ ሊሆን አይገባም፡፡

© 2010 by Third Millennium Ministries
www.thirdmill.org

በስነ-ምግባር የታነፀ ሕይወትን ለመምራት ጳውሎስ ያስቀመጠው ስልት በሁለት ወሳኝ መንገዶች ከሐሰት መምህራኑ ይልቃል፡፡ አንደኛ፣ የሚታመነው በእግዚአብሔር ኃይል እንጂ በሰው አቅም ላይ ባለመሆኑ ውጤታማ ነው፡፡ ሁለተኛ፣ ትኩረትን በኃጢአት እና በምድራዊ ነገሮች ላይ ከማድረግ ይልቅ በበጎ ምግባራት እና በመንፈሳዊ እሴቶች ላይ ስለሚያደርግ ውጤታማ ነው፡፡ የሚሰመርበት ጉዳይ ጳውሎስ የነደፈው ስልት ያዋጣል የሚለው ነው፡፡ ኃጢአትን ለመቋቋም ምንም ፋይዳ ከሌለው የብህትውና ልምምድ ይልቅ፣ ጳውሎስ ያቀረበው ስልት በስነ-ምግባር ታንፆ መኖር እንደሚቻል አረጋግጧል፡፡

ጳውሎስ ለቆላስይስ ሰዎች የጻፈው ደብዳቤ በሐሰት መምህራኑ የሚራገበውን አምልኮተ ጣዖት የተሞላ ኑፋቄ መፋለምን ያለመ ነው፡፡ የሐሰት መምህራኑ አምላክ የለሹ ህዝብ ከመንፈሳዊ ኃይላት ጋር የሚገናኝበትን እና ጽድቅን ለመቀበል ያዋጣዋል የሚሉትን መንገድ ጥብቅና ይቆሙለታል፡፡ ለእነዚህ ችግሮች ምላሽ ለመስጠት፣ ጳውሎስ ክርስቶስን ይሰብካል፡፡ ክርስቶስ ከሁሉ የሚበልጥ ጌታና ንጉሥ ነው፣ አገልጋዮቹም ከሁሉ ይበልጣሉ በማለት ያውጃል፡፡ በክርስቶስ ስለተገኘው ድነት እና በክርስቲያናዊ አኗኗር አማካይነት በኃጢአት ላይ ስለሚገኘው ወደር የለሽ እሴት ይሰብካል፡፡ በእያንዳንዱ ነጥብ ላይ፣ የሐሰት መምህራን ተስፋ ብቻ የሚሰጡበትን ጉዳይ እርሱ ግን ክርስቶስ ሰጠነ በማለት ግልጽ አድርጎ ያስቀምጠዋል፡፡

## 4. ዘመነኛው ተዛምዶ

እስካሁን ድረስ ጳውሎስ ለቆላስየይስ ሰዎች የጻፈውን ደብዳቤ ዳራ፣ አወቃቀሩንና ይዘቱን ስንመረምር ቆይተናል፣ አሁን ደግሞ፣ ትኩረታችንን ወደ ሦስተኛው ርዕሰ-ጉዳይ ማለትም ጳውሎስ ለቆላስይስ ሰዎች ወደ ጻፈው መልእክት ዘመነኛ ተዛምዶ ዘወር እናደርጋለን፡፡ እኛ፣ በዚህ ዘመን የምንኖር፣ ክርስቲያኖች ይህንን ጥንታዊ አስተምህሮ በሕይወታችን እንዴት እናዛምደዋለን?

ምንም እንኳን የጳውሎስን አስተምህሮዎች በዛሬው ሕይወታችን በትክክል ልናዛምድ የምንችልባቸው በርካታ መንገዶች ቢኖሩም፣ ጳውሎስንና ቀደምት ተደራሲኑን በእጅጉ ባሳሰቧቸው ሁለት የተዛምዶ ዓይነቶች ላይ እናተኩራለን፡፡ እነርሱም፡ ለክርስቶስ ብቻ ታማኝ ሆኖ የመዝለቅ አስፈላጊነት እና በዕለት ከዕለት ሕይወታችን በመንፈሳዊ ጉዳዮች ላይ ትኩረት የማድረግ ጠቀሜታ ናቸው፡፡ ለክርስቶስ ብቻ ታማኝ ሆኖ የመዝለቅን አስፈላጊነት በመመልከት እንጀምር፡፡

## ለክርስቶስ ታማኝ መሆን

በቆላስይስ ቤተክርስቲያን ውስጥ የነበሩ አማኞች፣ ለክርስቶስ ያቀርቡት የነበረውን አምልኮ ከሌሎች መንፈሳዊ ኃይላት አምልኮ ጋር እንዲቀላቅሉት ይበረታቱ ነበር፡፡ ምንም እንኳን እንዚህን መንፈሳዊ ኃይላት ኢጋንንቶች ናቸው ባይሏቸውም፣ አለን የሚሉት ኃይል፣ የቱንም ዓይነት ጥቅም አስገኙ ቢባል ምንጩ ከኢጋንንት ነው፡፡ እነዚህ ኃይላት ኢጋንንትም ይሆኑ ወይም ሰው ሰራሽ አማልክት፣ ወይም መላእክት፣ የቆላስይስ ሰዎች በምንም መንገድ ሊያመልኳቸው አይገባም፡፡ የሚያሳዝነው ግን፣ በመጀመሪያው ክፍለ ዘመን የነበረው ማኅበረሰባዊ ድባብ የቆላስይስ ሰዎች የጉዳዩን እውነታ እንዳይገነዘቡ ጫና ፈጥሮባቸዋል፡፡

በመጀመሪያው ክፍለ ዘመን፣ በሮማውያን ግዛቶች ውስጥ ተፅኖ ፈጣሪ የነበረው ሃይማታዊ አስተሳሰብ ብዙ አማልክት አምላኪነት ነበር፡፡ ያም ማለት፣ አብዛኛው ህዝብ ያምን የነበረው ብዙ አማልክቶችና መንፈሳዊ ኃይላት እንዳሉ ነበር፡፡ በግዛቶቹ ውስጥ ይኖሩ የነበሩ አብዛኞቹ የማኅበረሰብ ክፍሎች አማልክት አሉ ብለው

© 2010 by Third Millennium Ministries
www.thirdmill.org

ማመን ብቻ ሳይሆን ብዙ አማልክት አምላኪዎች ነበሩ፡፡ በዚያን ዘመን፣ በሮሜ ግዛት ውስጥ ይኖሩ ከነበሩት ህዝቦች ለአብዛኞቹ፣ በማኅበረሰቡ ባእድ አምልኮ ውስጥ ገናና የነበረውን ለምሳሌ፣ እንደ ዜየስ ዓይነቱን ጣዖት ፣ በተጨማሪም የየመንደሩን አማልክቶች እንዲውም በየቤቶቻቸውን ያስቀመጧቸውን አማልክቶች ማምለክ የተለመደ ነበር፡፡ እናም፣ ምንም እንኳን አማኞች እርሱን ብቻ እንዲያመልኩ ክርስቶስን ቢፈልግም፣ የቀደሙት ክርስቲያኖች ግን ሌሎችንም አማልክቶች እንዲያመልኩ ብርቱ ማኅበረሰባዊ ጉትጎታ ይፈጠርባቸው ነበር፡፡

በመሠረቱ፣ በመጀመሪያው ክፍለ ዘመን የሮሜ አገዛዝ ክርስቲኖችን ማሳደድ ሲጀምር፣ ዋናው ምክንያት ክርስቲያኖቹ ማኅበረሰቡ የተቀበለውን አምልኮተ-ጣዖት እውቅና ባለመስጠታቸውና አናመልክም በማለታቸው ነበር፡፡ ያቀረቡትም መከራከሪያ፣ ክርስቲያኖቹ ጣዖታቱን አላመልክ ካሉ ያስቆጧቸዋል፣ ስለዚህ፣ ክርስቲያኖቹ ተጠያቂ እንዲሆኑ ካላደረግን፣ ጣዖታቱ ጠቅላላውን የሮሜ ህዝብ ይቀጣሉ የሚል ነበር፡፡ ክርስቲያኖች ክርስቶስን ማምለክ እንዲያቆሙ ሮማውያኑ አላስገደዱም፣ ሆኖም ግን የሮሜ ጣዖታትንም ማምለክ አለባችሁ ነበር ያሉት፡፡

እንደ መጀመሪያው ክፍለ ዘመን የሮማውያን አስተሳሰብ፣ አንድ ሰው ምንም ዓይነት ታማኝነትን የማጉደል ስሜት ሳይፈጠርበት ብዙ አማልክትን ማምለክ ይችላል፡፡ ክርስቶስ ግን አምልኮ ለእርሱ ብቻ እንዲሆን ግድ ይላል፡፡ ክርስቶስን እናመልካለን ካልን፣ ሌላ ምንም ማምለክ አይገባንም፡፡ የቆላስይስ ሰዎቸ በእምነታቸው ጸንተው እንዲቆሙ ጳውሎስ ያሳስብ የነበረው ለዚህ ነበር፡፡ በቆላስይስ ምዕራፍ 1 ከቁጥር 21 እስከ 23 ድረስ እንዲህ ጽፏል፡-

> ***እናንተንም ነውርና ነቀፋ የሌላችሁና ቅዱሳን አድርጎ በእርሱ ፊት ያቀርባችሁ ዘንድ፥ በፊት የተለያቻሁትን ክፉ ሥራችሁንም በማድረግ በአሳባችሁ ጠላቶች የነበራችሁትን አሁን በሥጋው ሰውነት በሞቱ በኩል አስታረቃችሁ።***
> ***ይህም፥ ተመሥርታችሁና ተደላድላችሁ ከሰማችሁትም ከወንጌል ተስፋ ሳትናወጡ፥ በሃይማኖት ጸንታችሁ ብትኖሩ ይሆናል፤ ... (ቆላስይስ 1፡21-23)***

እኛ ለክርስቶስ ታማኝ ሆነን ካልዘለቅን፣ በእርግጥ ከእግዚአብሔር ጋር እንዳልታረቅን በራሳችን ላ መመስከራችን ነው፡፡ ከእግዚአብሔር ጋር ካልታረቅን ደግሞ፣ በወንጌል የተገለጠው ተስፋ ተካፋዮች አንሆንም፡፡ በቀላሉ ስናስቀምጠው፣ ለክርስቶስ ታማኝ ሆነን ካልዘለቅን፣ አልዳንንም ማለት ነው፡፡ ለክርስቶስ ታማኝ መሆን እጅግ ወሳኝ ነገር ነው፡፡

የሚያሳዝነው ግን፣ ዘመነኛው ዓለም የተለያዩ አማልክትን እንድናመልክ ግብዣን እያቀረበ ለክርስቶስ ያለንን ታማኘኝነት በተደጋጋሚ እየተገዳደረው መሆኑ ነው፡፡ በምሥራቃውያንም ዘንድ ብዙ አማልክት አምላኪነት የተለመደ ነው ለምሳሌ፣ ከቻይና ሦስት እውቅ ሃይማኖቶች አንዱ፣ ታዖይዝም፤ ከህንድ ሃይማኖት ዋነኛ የሆነው፣ ሂንዱይዝም፤ የጃፓን ባህላዊ ሃይማኖት የሆነው ሺንቶ ይጠቀሳሉ፡፡ በምዕራብውያኑ ዓለም ደግሞ፣ የአዲሱ ዘመን እንቅስቃሴ ከእነዚህ የምሥራቃውያን ሃይማኖቶች አብዛኞቹን የራሱ አድርጓቸዋል፡፡ ከዚህም ባሻገር፣ ሞርሞኒዝም እንደሚያስተምረው ሞርሞኖች በየዘመናቱ የሚፈጠሩ አማልክቶች ናቸው ይላል፡፡ ከዚያም ባሻገር፣ በአፍሪካ እና በእስያ የሚገኙትን የነገድና የጎሳ የተረታ ተረት ሃይማኖቶች ደግሞም በካሊፎርኒያ የሚገኘውን የሆሊውድ ሳይንስ አምላኪነት ጨምሮ ዝርዝሩ ማብቂያ የሌለው እስኪመስል በርካታ ጥቃቅን ብዙ አማልክት አምላኪዎች አሉ፡፡

© 2010 by Third Millennium Ministries
www.thirdmill.org

ከዚህ የባሰ ግን የዘመኑ ክርስቲያኖች ከተጨማሪ ችግሮች ጋር እየተጋፈጡ ነው፡፡ ለምሳሌ፣ አንዳንድ የዘመናችን መንግሥታትና ማኅበረሰቦች ክርስቲያኖች ለክርስቶስ ብቻ ታማኝ በመሆናቸው ምክንያት እያሳደዷቸው ነው፡፡ በህዝባዊት ሪፐብሊክ ቻይና የሚገኙት በርካታ አብያተ ክርስቲያናት በድብቅ የሚንቀሳቀሱት በዚህ ምክንያት ነው፡፡ በእስላማዊ መንግሥታት ያለው ስደት ደግሞ፣ እጅግ የከፋና ክርስቲያኖችን ለባርነት ግፋ ብሎም ለሞት የሚዳርግ ነው፡፡ እነዚህ ስደቶች አሰቃቂ ቢሆኑም፣ ሁኔታዎቹም እጅግ አስጨንቀው ጌታችንን እንድንክድ ቢገፋፉንም፣ ከእግዚአብሔር ጋር ታርቀን ለዘላለም መኖር ከፈለግን፣ እስከ መስዋዕትነት ድረስ በመጽናት ለክርስቶስ ታማኝ ሆነን መዝለቅ ይገባናል፡፡

በሌሎቹ የሰለጡኑ መንግሥታት ደግሞ፣ ክርስቲያኖች ጫና የሚደርስባቸው በክህደት መንፈስ ሲሆን፣ በእግዚአብሔርና በክርስቶስ ላይ ያላቸውን እምነት እርግፍ አድርገው እንዲተዉ ይገደዳሉ፡፡ ክርስትና እጅግ ኋላ ቀር እና የድንጋይ ዳቦ ዘመን እምነት እንደሆነና ከዘመኑ ሳይንሳዊ ሥልጣን ጋር እንደማይጣጣም ተደርጎ ይቆጠራል፡፡ የነገረ-መለኮትና የሳይንስ ትምህርት በበቂ ሁኔታ ያልቀሰሙ በርካታ አማኞች ለእነዚህ ተግዳሮቶች ተገቢ መልስ መስጠት ይሳናቸዋል፣ ስለዚህም እምነታቸውም ይናጋል፡፡

በሌላ ጎን ደግሞ፣ የዘመነኛው ዓለም ፍልስፋናዊ አንፃራዊነት የሃይማኖቶችን መቻቻል በእጅጉ እያበረታታ ነው፡፡ በውጤቱም፣ እውነትና ድነት ፍፁማዊ ናቸው የሚለው አቋም ይኮነናል ማለት ነው፡፡ ብቸኛው የድነት መንገድ ለክርስቶስ ታማኝ መሆን ነው በማለት ጳውሎስ በጽኑ ያስተምራል፡፡ በዘመኑ የምንኖር ክርስቲያኖች ይህንን ሃሳብ ስናንጸባርቅ፣ ግትሮችና መቻቻልን የማይፈቅዱ ተብለን እንፈረጃለን፡፡ ስለዚህ ዘላለማዊ በረከትን እናገኝባቸዋለን የሚባሉ ሌሎች መንገዶችን እውቅና እንድንሰጥ ማኅበረሰባዊ ጫና ያርፍብናል፡፡

ሁሉም ጫናዎች የሚመጡት ከቤተክርስቲያን ውጪ ብቻ አይደለም፡፡ ለምሳሌ፣ በአንዳንድ ለዘብተኛ የፕሮቴስታንት አብያተክርስቲያናት ውስጥ፣ የሴት አምላክ ተብላ ለምትጠቀሰው ለጥበብ ወይም ለሶፍያ ምሥጋና ይቀርባል፡፡ ሌሎቹ የፕሮቴስታንት አብያተክርስቲያናት ደግሞ በማኅበረሰባቸው ውስጥ የሚራገበውን ፍልስፍናዊ አንጻራዊነትን በመቀበል፣ በርካቶቹ እንዲያውም ሁሉም ሃይማኖቶች ክርስቶስን ባይቀበሉም እንኳን ወደ ድነት የሚያደርሱ መንገዶች ናቸወ ብለው ያስተምራሉ፡፡

እውነታው እንግዲህ የትም እንኑር የት፣ ለክርስቶስ ታማኝ እንዳንሆን የተለያዩ ጫናዎች የሚፈጠሩብን መሆኑ ነው፡፡ ጫናውም ሌሎቹም ሃይማኖቶችና ጣዖታት ዋጋ እንዳላቸው እንድንቀበልና የመጽሐፍ ቅዱሱን እግዚአብሔር እንድንክድ ማድረግ ነው፡፡ ይህም የሚመጣው፣ አንዳንድ ጊዜ ከመንግሥት፣ ከትምህርት ቤቶች፣ ከጎረቤቶቻችንና ከጓደኞቻችን፣ ከቤተሰቦቻችን ወይም ከቤተክርስቲያን መሪዎቻችንም ሊሆን ይችላል፡፡

ሆኖም ለጳውሎስ አስተምህሮዎች ታማኝ ሆነን መዝለቅ ከፈለግን ግን፣ እነዚህን ሁሉ አማራጮች ወዲያ ብለን ክርስቶስን ብቻ ምርጫችን ማድረግ ገባናል፡፡ ሊመለክ የተገባው ክርስቶስ ብቻ ነው፣ እውነተኛ ድነት እና መንፈሳዊ በረከቶችም የሚገኙት በእርሱ ብቻ ነው፡፡ ልክ እንደ ጳውሎስ፣ ከመጽሐፍ ቅዱሱ እግዚአብሔር ውጪ የሆኑ የመንፈሳዊ ኃይላትን አምልኮ በብርቱ ልንቃወም ደግሞም ከእግዚአብሔር ጋር እኛን ሊያስታርቅ የሚችለው ክርስቶስ ብቻ እንደሆነ በጽኑ ልናምን ይገባናል፡፡ የሐሰት ትምህርቶቹ የሚመጡት ከምንወዳቸውና ከምናከብራቸው ሰዎች፣ ከቤተክርስቲያኖቻችን መሪዎች ቢሆንም እንኳን ለክርስቶስ ባለን ታማኝነት በመጽናት አሻፈረኝ ማለት ይገባናል፡፡

© 2010 by Third Millennium Ministries
www.thirdmill.org

## መንፈሳዊ ትኩረት

ለክርስቶስ ብቻ ታማኝ ሆኖ የመዝለቅን ወሳኝነት ከተመለከትን አሁን ደግሞ ወደ ሁለተኛው ዘመነኛ ተዛምዶ ማለትም፡ በዕለት ከዕለት ሕይወታችን በመንፈሳዊ ጉዳዮች ላይ የማትኮርን ዋጋ ወደ መመልከቱ እንሸጋገራለን፡፡ ለምድራዊ ጉዳዮችም ስፍራ መስጠት አስፈላጊ ቢሆንም፣ ይበልጥ ተጠቃሚ የምንሆነው ግን ሕይወትን ከመንፈሳዊ አስተሳሰብ አንፃር ስንቃኘው ነው፡፡

በክርስቶስ ስናምን፣ ተአምራዊ ነገር በሕይወታችን ተከናውኗል ማለትም፣ ውስጣዊ ማንነታችን (መንፈሳችን) ታድሷል፡፡ ወደ እምነት ከመምጣታችን በፊት፣ ውስጣዊ ማንነታችን ሙት ነበር፣ ለእግዚአብሔር በጎ ምላሽ አንሰጥም ነበር፡፡ በእርሱ ላይ ኃጢአት በመሥራታችንና የእርሱ ፍርድ የሚገባን በመሆናችን ብቻ ሳይሆን፣ እርሱን በመጥላታችንና ለእርሱም ባለመገዛታችን የእግዚአብሔር ጠላቶች ነበርን፡፡ እግዚአብሔር እጅግ ስለወደደን ጠላቶች ሆነን እንድንቀር አልፈቀደም፡፡ ስለዚህ፣ መንፈሳችንን ሊድስ መንፈስ ቅዱስን ላከልን፣ ስለዚህም ውስጣችን ታደሰ፣ ኃጢአታችንን በመናዘዝ ለጌታ ፈጥነን መገዛት ደስ ያሰኘናል፡፡ ደግሞም፣ የእግዚአብሔር መንፈስ በውስጣችን አድሮ፣ ከክርስቶስ ያስተሳስረናል፣ ወደ ፊት በእርሱ የምንቀበለውን በረከትም ያረጋግጥልናል፡፡ ድነታችን በምድራዊ ፍላጎቶቻችን ላይ የተመሠረተ አይደለም፣ ነገር ግን በታደሰው መንፈሳችን መንፈሳዊ እውነታዎችና ከክርስቶስ ጋር ባለን አንድነት ላይ ነው፡፡ የቆላስይስ ሰዎች ምድራዊውን ነገር ቸል እያሉ በመንፈሳዊ ጉዳዮች ላይ ይበልጥ እንዲያተኩሩ ጳውሎስ የሚያበረታታው ለዚህ ነው፡፡

የነገረ-መለኮቱ ምሁራን ወደ እምነት ያልመጡትን ሰዎች ዳግመኛ ያልተወለዱ በማለት ይጠቅሷቸዋል፡፡ በተቃራኒው ደግሞ፣ ዳግመኛ የተወለዱ የሚለው ቃል ላመኑት ይጠቀሳል፡፡ እነዚህ ቃሎች የአንድ ሰው መንፈስ ወይም ነፍስ ያለችበትን ሁኔታ ያሳያሉ፡፡ ዳግም አለመወለድ ማለት በመንፈስ ሙት መሆን ሲሆን፣ ዳግም መወለድ ደግሞ በመንፈስ ሕያው መሆን ነው፡፡

ዳግም ያልተወለዱ ሰዎች በኃጢአታቸው ምክንያት በእግዚአብሔር ፍርድ ስር ናቸው፡፡ በተጨማሪም ምንም ዓይነት ሞራላዊ አቅም ስለሌላቸው፣ እግዚአብሔር እንከን የሌለባቸው ንፁሐን ብሎ እንዲጠራቸው የሚያደርግ ሥራ መሥራት አይችሉም፡፡ ከዚህም ባሻገር፣ እግዚአብሔር ንጹህ ናቸው የሚላቸውን ነገሮች የማድረግ ግብረገባዊ ፍላጎት የላቸውም፡፡ በአጭሩ፣ ዳግም ያልተወለዱ ሰዎች አልዳኑም፣ ራሳቸውንም ማዳን አየይችሉም በእግዚአብሔር አምነው መዳንም አይፈልጉም፡፡

በሌላ በኩል፣ ዳግም የተወለዱቱ የእግዚአብሔር ህግ በሚጠይቀው መሠረት ስለ ኃጢአታቸው ከሞተው ከክርስቶስ ጋር ከመስማማታቸው የተነሳ ይቅር የተባሉ ናቸው፡፡ ከዚያም ባሻገር፣ ያተደሰው መንፈሳቸው ሞራላዊ አቅም አግኝቷል፣ ስለዚህም እግዚአብሔርን መታዘዝ ይችላሉ፣ ግብረገባዊ መሻትም አላቸው ስለዚህም እግዚአብሔርን የመታዘዝ ፍላጎት አላቸው፡፡

ወደ እምነት ስንመጣ በውስጣችን የተካሄደውን የመንፈሳዊ ለውጥ ዋጋ ማጣጣል ከባድ ነው፡፡ ዳግም ልደታችን አዲስ ሰዎች አድርጎናል፡፡ እኛ ይቅር የተባልን ሰዎች ብቻ ሳንሆን፤ ትልቅ መንፈሳዊ ለውጥ ያገኘን ሰዎች ነን፡፡ ጳውሎስ በቆላስይስ ምዕራፍ 2 ቁጥር 13 እንደጻፈው ዳግም መወለድ መንፈሳዊ ለውጥ ነው፡፡

> ***እናንተም በበደላችሁና ሥጋችሁን ባለመገረዝ ሙታን በሆናችሁ ጊዜ፥ ከእርሱ ጋር ሕይወትን ሰጣችሁ፤ በደላችሁን ሁሉ ይቅር አላችሁ፤ (ቆላስይስ 2፡13)***

© 2010 by Third Millennium Ministries
www.thirdmill.org

እኛ ሁላችን በአንድ ወቅት በኃጢአት ምክንያት ሙት ነበርን፤ ማለትም በእግዚአብሔር ፍርድ ስር ነበርን፡፡ እግዚአብሔር ግን ኃጢአታችንን ይቅር አለን ሕያውም አደረገን፡፡ በኃጢአተኛው ተፈጽጥሯችንም ምክንያት ሙታን ነበርን፤ ማለትም ከፉት የሚቀናው ተፈጥሮ ነበረን ስለዚህ ምንም ዓይነት ግብረገባዊ መሻት አልነበረንም፡፡ አሁንም እንደገና፤ እግዚአብሔር ሕያዋን አደረገን፡፡ በውጤቱም፤ እኛ አሁን መልካሙን የመመኘትና መልካሙን የማድረግ መሻት አለን፡፡

አሮጌውና ዳግም ያልተወለደው መንፈሳችን ምንም ዓይነት ሞራላዊ ናፍቆትና አቅም የለውም፡፡ የታደሰው መንፈሳችን ግን ሞራላዊ አቅሙም መሻቱም አለው፡፡ ዳግም ተወልደን ከንጉሡ ከክርስቶስ ጋር አንድ ከመሆናችን አስቀድሞ በመንፈስ ሙታን በነበርን ወቅት፤ ምንም እንኳንበውስጣችን ፍላጎት ቢኖርም፤ በመንፈሳዊ ነገሮች ወይም "በላይ ባሉት ነገሮች ላይ" ማትኮር ፋይዳ ቢስ ይመስለን ነበር፡፡ አሁን ግን ዳግም በመወለዳችን፤ ለማድረግ እጅግ ደስ የሚያሰኝን ነገር በአዲሱ ሕይወታችን ላይ በማትኮር በአዲስ መንገድ ነገሮችን ማከናወን ነው፡፡ መንፈሳችን ሕያው ሆኗል፤ አሁን መንፈሳውያን ሰዎች ሆነናል፡፡ እጅግ አመክኖአዊ፣ ያለ ምንም ጭንቀት የምናከናውነው፤ ለእኛ እጅግ ጠቃሚ የሆነው እና እንደ መንፈሳውያን ሰዎች የምናከናውነው ተግባር በመንፈሳዊ ሕይወታችን ላይ ማትኮር ነው፡፡ ጳውሎስም በቆላስይስ ምዕራፍ 3 ከቁጥር 1 እስከ 2 ድረስ እንዲህ በማለት ቀጣይ ማሳሰቢያውን ይለግሰናል፡

> ***እንግዲህ ከክርስቶስ ጋር ከተነሣችሁ፥ ክርስቶስ በእግዚአብሔር ቀኝ ተቀምጦ ባለበት በላይ እሹ፤***
> ***በላይ ያለውን አስቡ እንጂ በምድር ያለውን አይደለም። (ቆላስይስ 3፡1-2)***

ከክርስቶስ ጋር በላይ ስለተቀመጥን፤ ልቡናችን ማተኮር ያለበት ለሰማይ አግባብነት ባለው ነገር ላይ ነው፡፡ አሁን ስለ ፍጥረተ ዓለሙ የሥልጣን አወቃቀር ትክክኛ ግንዛቤ አግኝተናል፤ ዓለም እንዴት እንደምትንቀሳቀስ ደግሞም ትክክለኛ በረከትን የሚያስገኙት ምን ነገሮች እንደሆኑ ተረድተናል፡፡ ይህም እውቀት ሕይወታችን የምንመራበትን አቅጣጫ ቀይሮታል፡፡

በአንድ የታሪክ ዘመን ግን፤ ጳውሎስ በሰማያዊ ነገሮች ላይ እንጂ በምድራዊ ነገሮች ላይ ማትኮር የለብንም ብሎ የተናገረውን ንግግር ክርስቲያኖቸ በተሳሰተ መንገድ ተርጉመውት፤ ሰማያዊ ነገርን በሙላት ለማግኘት መደበኛውን ሰብዓዊ ሕይወት ቸል ማለት አለብን ማለቱ ነው ብለው ነበር፡፡ ለዚህ ዓይቱ አስተሳብ በመካከለኛው ክፍለ ዘመን የነበሩት ባህታውያን መነኩሴዎች ትክክለኛ ምሳሌዎች ናቸው፡፡ አንዳንዶቹ ባህታውያን፤ ከተቀረው ማኅበረሰብ ተገልለው ይኖሩ ነበር፡፡ አንዳንዶቹ ደግሞ ለረጅም ጊዜያት በዋሻዎችና በበረዶአማ ተራሮች ጫፍ ላይ ኖረዋል፡፡ ሌሎቹ ደግሞ በራሳቸው ላይ አካላዊ ጉዳት አድርሰዋል፡፡ በመንፈሳዊ ሕይወት ለማደግና ከዚህ መንፈሳዊነት ከኀደለው መደበኛ ዓለም መገላገል የሚቻለው በዚያ ነው ብለው በጽኑ ያምኑ ነበር፡፡ እንዲያውም፤ በአንዳንድ ሁኔታዎች፤ በቆላስይስ ይኖሩ የነበሩ የሐሰት መምህራን ይፈጽሟቸው የነበሩ ስህተቶችን ይፈፅሙም ነበር፡፡

እውቁ አስተማሪና በአሁኑ ወቅት ቱስኬጂ ዩኑቨርሲቲ በመባል የሚታወቀው ዩኒቨርሲቲ መሥራች ቡከር ቲ. ዋሽንግተን የሚከተለውን የአሜሪካኖች ምሳሌ መስሏል ይባላል፡

> *አንድን ወደ አዝቅት የጠለቀን ሰው መያዝ ያማረው ሰው አብሮት አዝቅት ውስጥ ካልገባ ሊይዘው አይችልም፡፡*

© 2010 by Third Millennium Ministries
www.thirdmill.org

ጳውሎስ ስለ ክርስቲያኖች ውስጣዊ ሕይወት ያስተማረውን ነገር፣ ዋሽንግተን ከሰው ሰብዓዊ ግንኙነት ጋር አዛምዶ አቅርቦታል፡፡ ማለትም የተፈለገው፣ ጉልበታችንንና ትኩረታችንን ሁሉ ኃጢአት ናፋቂ የሆነውን መሻታችንን በመጫን ላይ ካሳረፍን፣ አሁንም እያተኮርን ያለነው በክፉ መሻቶቻችን ላይ ነው ማለት ነው፡፡ አዎን፣ መልካም ሥራ ቢመስልም እንኳን፣ ኃጢአትን አሻፈረኝ ማለት ግሩም ነገር ነው፡፡ ጳውሎስም ኃጢአትን ተሞሉ ሥጋዊ መሻቶቻቸውን እንዲገድሉ አማኞችን አበረታቷል፡፡ ጳውሎስ በቀላሉ ሊያስጨብጥ የፈለገው ነጥብ ግን ምድራዊ ጉዳዮችን የምናይበትን እይታ በአዲስ መንገድ መቀየር ይገባናል፤ ያንን ስናደርግም ደግሞ ትኩረታችንን ከምድራዊ ነገሮች ዘወር በማድረግ በመንፈሳዊ ነገሮች ላይ ማድረግ ይገባናል የሚል ነው፡፡ ሆኖም ጳውሎስ የጠቀሳቸው "መንፈሳዊ" ወይም "ሰማያዊ" ጉዳዮች በዚህ ዓለም በመኖር የምንገልጣቸው ናቸው፡፡ በቆላስይስ ምዕራፍ 3 ከቁጥር 12 እስከ 16 የተናገራቸውን ቃላት እናድምጥ፡-

> ***እንግዲህ እንደ እግዚአብሔር ምርጦች ቅዱሳን ሆናችሁ የተወደዳችሁም ሆናችሁ፥ ምሕረትን፥ ርኅራኄን፥ ቸርነትን፥ ትህትናን፥ የዋህነትን፥ ትዕግሥትን ልበሱ፤ እርስ በርሳችሁ ትዕግሥትን አድርጉ፥ ማንም በባልንጀራው ላይ የሚነቀፈው ነገር ካለው፥ ይቅር ተባባሉ፤ ክርስቶስ ይቅር እንዳላችሁ እናንተ ደግሞ እንዲሁ አድርጉ፤ በእነዚህም ሁሉ ላይ የፍጻሜ ማሰሪያ የሆነውን ፍቅርን ልበሱት። በአንድ አካልም የተጠራችሁለት ደግሞ የክርስቶስ ሰላም በልባችሁ ይግዛ፤ የምታመሰግኑም ሁኑ። የእግዚአብሔር ቃል በሙላት ይኑርባችሁ፤ በጥበብ ሁሉ እርስ በርሳችሁ አስተምሩና ገሥጹ፤ በመዝሙርና በዝማሬ በመንፈሳዊም ቅኔ በጸጋው በልባችሁ ለእግዚአብሔር ዘምሩ፤ (ቆላስይስ 3፡12-16)***

ወደ ፍሬ ነገሩ ስንመጣ፣ ጳውሎስ እያለ ያለው፣ በሕይወታችን "ሰማያዊ" ወይም "መንፈሳዊ" የምንላቸው ጉዳዮች በሰማያት የተገለጠችው የእግዚአብሔር መንግሥት በዚህ በምድር የምትታወቅባቸው ጉዳዮች ናቸው ነው፡፡ በሌላ መንገድ ስናስቀምጠው ደግሞ፣ ሰማያዊ አስተሳሰብ ማለት ክርስቶስ ተብሎ በሚጠራውና ወደ ሰማይ በወጣው ላይ ማትኮርና በዚህ በምድር ይበልጥ እርሱን እየመሰልን የምንሄድባቸውን የሕይወት ዘይቤዎች መከተል ማለት ነው፡፡

ጳውሎስ "ሰማያዊ" ወይም "መንፈሳዊ" እያለ ከጠቀሳቸው ነገሮች አብዛኞቹ፣ ከሰዎች ጋር ካለን ግንኙነት ጋር የተያያዙ ናቸው፣ እንዲያውም አንዳንዶቹ ከሰዎች ጋር ባለን ግንኙነት ብቻ ሊገለጡ የሚችሉ ናቸው፡፡ ለምሳሌ፣ ርኅራኄ፣ ገርነት፣ ትኅትና፣ ጨዋነት፣ ትዕግሥት፣ ይቅርታ፣ ፍቅር እና ሰላም ሊገለጡ የሚችሉት በማኅበረሰብ አውድ ውስጥ ነው፡፡ እነዚህ የሕይወት ዘይቤዎች አሁን በዚህ ዓለም በመኖር የምንገልጣቸው ናቸው፡፡

እንዲውም ጳውሎስ፣ በቆላስይስ ምዕራፍ 3 ከቁጥር 16 እስከ ምዕራፍ 4 ቁጥር 6 ድረስ፣ አማኞች እነዚህን የሕይወት ዘይቤዎች ተግባራዊ ሊያደርጉ የሚችሉባቸውን በርካታ ምድራዊ ዝምድናቸው ማብራሪያ ሰጥቶባቸዋል፡፡ ለምሳሌ፣ አማኞች በመዝሙር፣ በመንፈሳዊ ቅኔና በውዳሴ እርስ በርስ ሊማማሩ እንደሚገባቸው ጽፏል፡፡ ሚስቶች ለባሎቻቸው እንዲገዙ፣ ባሎች ደግሞ ሚስቶቻቸውን እንዲወድዱ አዝዟል፡፡ ልጆች ወላጆቻቸውን እንዲታዘዙ፣ ወላጆች ደግሞ ልጆቻቸውን እንዲያበረታቱ መመሪያ ሰጥቷል፡፡ በሮች ደግሞ፣ ታዛዥና ትጉ እንዲሆኑ፣ ጌቶች ደግሞ የሁላችን ጌታ የሆነው ጌታ ቤተክርስቲያንን እንደሚያይበት እይታ ባሮቻቸውን እንዲመለከቱ አሳስቧል፡፡ እርሱ ራሱ ደግሞ ወንጌልን በሚሰብክበት ወቅት እግዚአብሔር እንዲያበረታው እንዲጸልዩለት ጠይቋል፡፡ የቆላስይስ ሰዎችም ወንጌልን የሚሰብኩበትን እድል ሲያገኙ በጥበብና

በትጋት እንዲቀሙበት መመሪያ ሰጥቷቸዋል፡፡ እነዚህ ሁሉ መመሪያዎች ከ"ሰማያዊ" ወይም ከ"መንፈሳዊ" ጉዳዮች ጋር ትስስር አላቸው፡፡ ሁሉም በተግባር ሊገለጡ የሚችሉት ግን በዚህ በአሁኑ ዓለም ነው፡፡

ለጳውሎስ፣ ሰማያዊ ወይም መንፈሳዊ ልቡና መያዝ ማለት መንግሥተ ሰማያት አሁን እዚህ በምንኖረው ኑሮ ምን ያህል አስደናቂ እንደሆነች ማሳየትና ይህች ዓለም የመንግሥተ ሰማያት መልክ እንዲኖራት ለማድረግ የሚያግዙ መንገዶችን መፈለግ ማለት ነው፡፡ ያም ተግባራዊ የሚሆነው በአዲሱ መንፈሳዊ ማንነታችን ላይ ስናተኩር፣ እና ከዚያ ማንነት ጋር የሚጣጣም መልካም ሥራ ስንሠራ ነው፡፡ በላይ በሰማይ ዘወትር የሚከናወኑትን መልካም ሥራዎች በዚህ በምድር መሥራት ማለት ነው፡፡ ሌሎችን መውደድ፣ ሌሎችን ይቅር ማለት፣ ደግ፣ ጨዋና ትጉት መሆን ማለት ነው፡፡ ሌሎችን ሰዎች ኢየሱስ በሚያያቸው መንገድ ማየት ማለት ነው፡፡ በአጭሩ፣ ትኩረትን በመንፈሳዊ ጉዳዮች ላይ ለማድረግ፣ አሁን፣ እዚህ፣ በዚህ ምድር ላይ የእግዚአብሔርን መንግሥት በመገንባት ላይ ልናተኩር ይገባናል፡፡

## 5. ማጠቃለያ

በዚህ ጥምህርት በሐዋርያው ጳውሎስና በቆላስይስ አማኞች መካከል የነበረውን ግንኙነት በጥልቀት ተመልክተናል፡፡ ጳውሎስ ለቆላስይስ ሰዎች የጻፈውን ደብዳቤ ዳራ፣ አወቃቀሩንና ይዘቱንም መርምረናል፡፡ በመጨረሻም፣ የቆላስይስ ሰዎች ከጳውሎስ የተላለፈላቸውን አስተምህሮ ዘመነኛ ተዛምዶ ተወያይተንበታል፡፡

ጳውሎስ ለቆላስይስ ሰዎች ከጻፈው ደብዳቤ ዛሬ ለእኛ በርካታ ትምህርቶችን እናገኛለን፡፡ ስለ ክርስቶስ የበላይነት፣ ለእርሱ ሐዋርያትና ለአስተምህሮአቸው ትልቅ አክብሮት እንዲኖረንም ያስተምረናል፡፡ በእግዚአብሔር መንግሥት እኛ የሚኖረንን ድርሻ እና አሁን እያጣጣምን ያለነውን ታላቅ መዳን ያብራራልናል፡፡ ከሰማያዊ ጥሪ ተካፋይ እንደሆኑ ህዝቦች፣ በመንፈሳዊ አስተሳሰብ እንድንኖር ደግሞም ሰማያዊ እሴቶችን በምድር ለመግለጥ እንድንተጋ ያበረታታናል፡፡ በክርስትና ሕይወታችን ወደፊት እየገፋን ስንሄድም፣ ጳውሎስ በዚህ መልእክቱ ያስተላለፋቸውን መልእክቶች ማስታወስ እምነታችንን በጽናት እንድንጠብቅ፣ እንደ ፍሬያማና የተባረኩ የእግዚአብሔር መንግሥት ሕዝቦች እንድንኖር ይረዳናል፡፡

© 2010 by Third Millennium Ministries
www.thirdmill.org